# ሰው እና ሰው

## አጫጭር ልብወለድ ታሪኮች

ከፀሐዬ መሠለ

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሐንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
Kuraz Publishing Agency
112719 30933
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa. Ethiopia

መጀመሪያ ሕትመት 1985

የሽፋን ስዕል ብርሃነሕይወት ጌታቸው

# ማውጫ


| ተ.ቁ | ይዘት | ገጽ |
|---|---|---|
| 1 | ሰውና ሰው | 5 |
| 2 | ንቃት—ንቃቃት | 28 |
| 3 | ባለ—ጉዳይ | 46 |
| 4 | የማከያው ጥያቄ | 65 |
| 5 | 'ወሬ ከማሪው' | 84 |
| 6 | የእንጀራ ገመድ | 107 |
| 7 | ጥብቅ መመሪያ | 137 |
| 8 | ሥጋ ብያት | 151 |

# ሰውና ሰው

የእጅ መዳፍ በምታክለው ክብ ፊቱ ላይ ተጐልጉለው የሚታዩት የቀያይ ዓይኖቹ ፈጣን እንቅስቃሴ ከጦር ሜዳ ተሸንፈው የተመለሱ ወታደሮቹን የሚገላምጥ ባሻ ያስመስሉታል ። እንደ ጠወለገ የጐመን ቅጠል የተዝለፈለፉትን ቀርበታ ጆሮዎቹንና ቀጥ ብሎ የወረደውን ረጅም አፍንጫውን ከስንዝር ቁመቱ ጋር ያመዛዘነ ሳቅ ይመጣበታል ። እስከጆሮዎቹ በሚደርሰው የአፉ ቅድ አልፎ አልፎ ብቅ የሚሉት ጥርሶቹ ሰነፍ ገበሬ ያቆመውን አጥር በሞዴልነት የሚገልጹ ናቸው ። ገምቦ ጭንቅላቱን ከደቃቃ ሰውነቱ ጋር ያገናኘው አንገቱ ፡ በዳበሳ ካልሆነ ማየት አዳጋች ነው ።

ሲጋራ ከአፉ ፡ ብዕር ከጣቶቹ አይለይም ። የሚጽፈው ጠረጴዛው ላይ ተደፍቶ እንደመሆኑ የሚራመደውም ወደ ኋላው ከፉኛ ተለጥጦ ስለሆነ ኩሩ ያስመስለዋል።

ነጋ ጠባ ፡ ከግራ ከቀኙ ፡ ከፊት ከኋላው ተቀልሎ የሚጠብቀውን ፋይል ሲያገላብጥ ይውላል ። መዝገብ ቤቱ አንዲት መስኮት እንኳ የለውም ። በዚህ ላይ የሚበንበት አቧራ ለጉድ ነው ። እናም አይኖቹ ተዳክመዋል ። ይህን ችግሩን በተደጋጋሚ ለሚመለከታቸው ቢያቀርብም ሲያፌዙበት "በእቅድ ተይዟል! ባጀት ሲፈቀድልን እንደሚሆን እናደርግልሃለን" ከማለት ወዲያ የፈየዱለት ነገር የለም ።

አይኖቹን ለመርዳት ሲልም የጠርሙስ ቂጥ የመሰለ መነፅር መደንቀር ከጀመረ አሥራ አራት ዓመት አልፎታል ። ያም ቢሆን በሀኪም የታዘዘለት አይደለም ። ጽሑፍ አጉልቶ ስለሚያሳይ ብቻ የሚች ጉረቤቱን የቄስ ማህደረ ሥላሴን መነፅር ከባለቤታቸው ከወይዘሮ መርአዊት ላይ በሦስት ወራት ክፍያ በሃያ አምስት ብር ገደማ ገዝቶ ይጠቀምበታል ። ታዲያ ይኸው መነፅር ለደከሙት ዓይኖቹ እገዛ ቢያደርግለትም ፡ "ዶክተር"ና "ፕሮፌሰር" በተሰኙ የስም ቅጥያዎች የከረረ ፌዝ አስከትሎበታል ።

ለሥራ ሲገባ ከሁሉም ሠራተኛ ቀድሞ ፡ ከሥራ ሲወጣም ከሁሉም ዘግይቶ ነው ፤ ከማንም ጋር ላለመገናኘት። በተለይም በፋይናንስ መምሪያ ውስጥ ያሉት ወጣት ኤክስ ፐርቶች ካገኙት ሠላም አይሰጡትም ።

ዘመናዊ ትምህርት ቤት ገብቶ እውቀት አልቀመሰም ። ለማስረጃነት የሚያገለግለው አንድም ሰርቲፊኬት የለውም ። አፈር ይቅለላቸውና የላሊበላው መሪጌታ ክንፉ ትምህርት ነው አሁን ለሚገኝበት ሥራ ያበቃው ። ድሮ ማንበብና መፃፍ የሚችል ሥራ የማግኘት ዕድሉ ሰፊ በነበረበት ጊዜ ነበር በዚሁ መስሪያ ቤት በተላላኪነት የተቀጠረው ። በተማሪነቱ ዘመን ቅኔ ሳይዘርፍ አልቀረም ፡ ጥሩ ገጣሚ ነው ። አዘውትሮ አይፃፍ እንጂ ፡ አልፎ አልፎም ቢሆን ቆሎ በሚመስለው አጣጣሉ የሚያስፍራቸውን ግጥሞቹን የሚያነቡለት ያደንቁታል ። በተላላኪነት አሥራ አምስት ዓመት ያክል እንደሠራ ፡ የማንበብና የመፃፍ ችሎታው ተመዝኖና የሥራ ትጋቱ ታይቶ በዕድገት ወደ ረዳት መዝገብ ቤት ፀሐፊነት ተዛውሮ



ደመወዙም 127 ብር ደረሰለት ።

ታዲያ ኤክስፐርቶቹ ይህንን እያወቁ "ስኮላር ሞልቶሃል ወይ?...መምሪያ ሃላፊ ለመሆን ታጭተሃል...ለሚኒስትርነት ትታማለህ..." እያሉ ያሾፉበታል ። በሌላ ቀን ደግሞ "ከሹመት ጋር ወደ ሌላ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ልትዛወር ስለሆነ ለመሸኛ ግብዣ አዋጡ እየተባልን ነው... የመዝገብ ቤት ማስትሬትህን ያገኘኸው ከኢስት አንግልያ ዩኒቨርሲቲ ነው ይባላል ።..." በማለት ከላዩ የማይነጥለውን አሮጌ ነፍስ ይማር ኮቱን እየጎተቱ እረፍት ይነሱታል ። ይስቁበታል ። ይቀልዱበታል ። እያከበሩቸው ፡ ይዘልፉታል ። እየፈራቸው ፡ ይደፍሩታል ። ከአለባበሱ ጀምሮ እስከ ተፈጥሮው አቃቂር እያወጡ ፡ በአራዳ ቋንቋ እያፌዙ ጊዜ ያሳልፉበታል ። እርሱ ግን ሲታመሙ ይጠይቃቸዋል ። አደጋ ሲደርስባቸውም ከልቡ ያዝንላቸዋል ። በፀሎቱም ምህረት ይለምንላቸዋል ።..

አንድ ቀን ጠዋት ፡ የዕለት ሥራ ስላልነበረው ፡ እንደ ትላንት ዕፎ የጨረሰውን ዶሴ መልሶ ይገለብጣል ። በዚህ ጊዜ የመዝገብ ቤቱ ዋና ሹም ፀሃፊ የከንፈር ቀለም ካልቀባሁህ እያለች እየታገለችው ፡ ሁለት ጆሮዎቹን ወደላይ እየጎተተች ካስካካችበትና ከቀለደችበት በኋላ "አቶ በድሪ በአስቸኳይ ጠርተውሃል" ብላው ፈንዳራ መቀመጫዋን እያነጠረችበትና በሹል ተረከዛም ጫማዋ ወለሉን እያስጮኸችበት ወጣች ።

ሰውነቱ በላብ ዝፍቅ አለ ። አቶ በድሪ የሚጠሩት ለቁም ነገር ቢሆንም ብዙ ከቀለዱበት በኋላ ነው ቁምነገሩን

የሚነግሩት ። የሁሉንም ቀልድ ባይወዱም የሳቸው ደግሞ በጣም ያስጠላዋል ። ድርቅ ያለ ቀልድ ነው ። ራሳቸው ተናግረው ከጣራ በላይ ይስቃሉ ።

ላለመሄድ ፈልጐ ነበር ። እምቢተኛነት መሰለው ። የበላይ ሀለቃን ትዕዛዝ ቢጥስ ከሙሴ ህጐች አንዱን እንደጣሰ ይሰማዋል ። የሙሴን ህጐችን በጥብቅ የሚያከብረውን ያኽል አለቃውንም ያከብራል ።

በፋይል ከተጨናነቀው ቢሮው ወጥቶ አቶ በድሪ ወደሚገኙበት ክፍል ሲያመራ አራት ወጣት ሠራተኞች አገኙት ።

"ታዲያስ ጓድ ከፍያለው?" አለው ከወጣቶቹ አንዱ ።

"ክብሩ ይስፋ !" ሲል መለሰለት ፤ ሁለት እጆቹን ዘርግቶ ወደላይ እያንጋጠጠ ። ሁሌም ቢሆን እንጋጦ ነውና የሚራመደው ለስሙ ያህል ተንጠራራ እንጂ ተመልካች አልተገነዘበለትም ።

"የት ነህ?"

"አቶ በድሪ ዘንድ !"

ኮቱን ወደኋላ እየጐተቱ ፤ ጭንቅላቱን እየደባበሱ ፤ እየሣቁ፤እያውካኩ ለጥቂት ርቀት ካጀቡት በኋላ ተለዩት ።...

የአቶ በድሪን ቢሮ አንኳኩቶ ከፍቶ እንደገባ ከወገቡ ጐንበስ ብሎ እጅ ነሳ ። አቶ በድሪ የወትሮውን ቀልዳቸውን አልወረወሩም ። ድምቡሼ ፊታቸውን አኮሳትረው ፤ እሳት ጐርሰው ነበር የጠበቁት ።

"ቅሌታም ወራዳ ! አንተ በኛ ላይ ልታፌዝ ያምርሃል ? ሜርድ !..." ከፍ ዝቅ አድርገው ሰደቡት ።



"በህግ !... በባንዲራው ! ... በመንግስት አምላክ !..." አላቸው ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ ።

"ለበዓል የሚቀርብ ፅሁፍ አዘጋጅ ብትባል ይህንን ነው የምትወረውርልን ? ጅላንፎ !"

"በህግ ! በባንዲራው !..." አላቸው እየተንቀጠቀጠ ።

"አንበው እስኪ ጮክ ብለህ !" በማለት አንድ ወረቀት ሊያቀብሉት እጃቸውን ዘረጉ ።

"ጌታዬ ! የፈለጉትን ይጠይቁኝ ።... ግን አይስደቡኝ ... እንደናንተው ሰው ነኝ ። እንደ ሁሉም ሰው በአርአያ ሥላሴ ነው የተፈጠርኩት ። ሰውን መስደብ እኮ..."

አላስጨረሱትም ።

"ይህንን ግጥም ብለህ ለምን ፃፍክ ?"

"የታየኝን ብያለሁ !"

"እንዴት የታየኝን ?" ጣታቸውን ቀሰሩበት ።

"ባይጥምዎት ቀደው አይጥሉትም ? ለርስዎ የሚጥም ልጽፍ ዋስ አልጠራሁ..." አለ ፤ እንዴት እንደሚያስረዳ እየጨነቀው ።

"ላንብልህ አድምጥ !" አሉና በረጅሙ ተነፈሱ ።

በግራ እጃቸው የግራ አገጫቸውን ደግፈው ፤ በቀኝ እጃቸው ወረቀቱን ራቅ አድርገው ይዘው ማንበብ ጀመሩ ።

## “ዝምታ – ዕድሜ ቀጥል መላ”

*ከት ከት ብሎ ሳቀ – የባህር ማሽላ*
*....*
*– የአበው ብሂል*
*– ማን ይቅር ሊል?*
*ጥንትም – ያው ነበር ደንቡ ፣*
*– አለመድረሻ መጋለቡ ።*
*እኔ እኔ እያሉ ከተሞላቀቁ ፣*
*መች ይቀራል – ትንቅንቁ!*
*አንቺስ ብትሆኝ!*
*ማነሽ ቢሉሽ … ማነኝ ልትይ?*
*የዕለት እንጀራሽን … ስታበስይ፣*
*አበባ ተገኘሽና … እሾህ ውስጥሽ!*
*በይሁን ይሁን … ሆታ ሲወርድልሽ ፣*
*ባንቺ ያዘኑ … “ኤዲያ !” ያሉሽ*
*“አበባዩ ሆይ – ለምለም” ሲሉሽ ፣*
*– ቅር የማይልሽ!*
*ሆድ ለሆድ!…*
*ለማታውቂን – ለምናውቅሽ ፣*
*ቅምጥሎችሽ – እንዳሻቸው ፣*
*“እኛ ! እኛ!” – ለራሳቸው ፣*



*ሲሉን – ዝም አልሻቸው?*
*“አበባዩ ሆይ …!” – እስቲ አድምጪን ፣*
*“ሆ ብለን መጣን…! – ሆ!” ብለን ፣*
*– ስንዘፍንልሽ ፣*
*ምን ሊሉን ነው – ቅልቦችሽ?*
*— ጦር ሊሰብቁብን*
*— ስድብ ሊያወርዱብን ?*
*– ጠይቂያቸው!*
*– ዝም አትበይ – ከለላ ጉጅአቸው ።*

* * *

አንበው እንደጨረሱ ዓይኖቻቸውን አጉረጠረጡበት ።

“ታዲያስ! ማን ፃፈው?” አሉት

“እኔ … እ…እ…” ለጋ ቅቤ እንዳላሱት ሀፃን ተንተባ ተበ ።

“ትርጉሙ ምንድነው? ምን ግንኙነት አለው ከበ ዓሉ?”

የሚመልሰው ጠፋው ። ግጥሙን ዕሮ ሲሰጥ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ይመጣብኛል የሚል ግምት አልነበረውም ። ቁጭት አደረበት ። የዛሬን ብቻ መውጪያ እንዲያገኝ ፈጣሪውን ተማፀነ ።

“ትርጉሙ ምንድነው? አትናገርም?” አምባረቁበት ።

“ትርጉም የለውም ብለው ምነው አይጥሉትም?”

“ወረቀቱ አይጣልም! ማስረጃ ነው ።”

“አሁን ምን ፍጠር ይሉኛል?”

“ፖለቲካ ጀመርክ አይደል? ቆሎ ያረረብህ የዜች ዓለም

መናጢ ድሃ መሆንክን ዘንግቲህ … አንተ ብሎ ባለቅኔ!… ቆይ!…”

“ኧረ! … በስመአብ ይበሉ ጌታየ!… ደግም አልተና ገሩ። የምን ፖለቲካ አመጡ! ስብሃት ለአብ…” አማተበ ።

“ጌት አውት!” አሉት ጠረጴዛውን በቡጢ ዱ. እያደ ረጉ ።

“ኧረ በቅዱስ ላሊቢላ!”

“ውጣ!”

ቆሌው እንደተገፈፈ አቀርቅሮ ወጣ ።…

* * *

“የደመወዝ ዕድገት አገኘሁ እንዳትለኝ!” በማለት ገና ከመግባቱ ፀሐፊዋ ለከፋዋን ጀመረችው ።

ፋይሎች ከዋጡት ጠረጴዛው አጠገብ የተቀመጠው ፍዝዝ እንዳለ ነበር ። መንፈሱ እንኳ ሁልግዜም እንደቀዘቀዘ ነው ። ጀምሮት የነበረውን ዕሁፍ ግልበጣ ወደጐን ገፋ አድርጐ አመት ሙሉ ከደመወዙ አጠረቃቅሞ የገዛውን አሮጌ ሮመር ሰዓት ተመለከተ ። ስድስት ሰዓት ይላል ።

ለምሣ የመውጪያ ሰዓት ቢሆንም ዘግይቶ መውጣት ነበረበት ። ስድስት ከሩብ ላይ ግስላ ሲጋራውን ለኩሶ ፡ በራ ጭንቅላቱ ላይ ብን ብን የሚሉ ፀጉሮቹን እየደባበሰ ወደ ቤቱ ገሠገሠ ፡ ለምሳ ።

ምግብ የሚያዘጋጁለት ሴትዮ ቤቱንም ያከራዩት ናቸው ። እንደፈለጉ ያዙበታል ። እፍ ቢሉት የሚበር ዓይነት እንጀራ በድቁስ አቅርበውለት አንድ ብር ያስመዘግቡታል ።



ቃል አይመልስላቸውም ። በሃያ ብር የተከራያት ጠባብ ክፍልም ብትሆን የሳቸው ናት ማለት ይቻላል ፤ የእትየ ወርቄ። ከአገር ቤት እንግዶች ሲመጡባቸው ፈቃድ ሳይጠይቁት በዚያች ጠባብ ክፍል ያሰፍሩበታል ።

“ምሣ’ትየ ወርቄ!” አላቸው ፤ ርጥብ እጁን እያሻሸ ።

“ቀስ! ምነው… ምን መጣ?”

ቂጣ አይሉት እንጀራ ፣ የተሰነጣጠቀ ጉድ ፣ ባልፈላ ሽሮ አቀረቡለት ። ወጉ እንዳይቀርም የወይፈን ቀንድ የሚያክል ቃሪያም ሰሀኑ ላይ አጋድመውለታል ። የከርስ ነገር ነውና ከርሱን መሙላት ጀመረ ።…

ሰዓቱን ሲመለከት ስድስት ተኩል ይላል ። መስሪያ ቤቱ ለመድረስ በቂ ግዜ እንዳለው እያሰበ እጆቹን ታጠበና ግድግዳው ላይ በተሰቀለው የአሮጌ ቀሚስ ትልታይ የረጠቡ እጆቹን አደራረቀ ።

ግስላ ሲጋራውን የወይራ ፍም ላይ ለኩሶ አረፍ አለ ፤ መዘዝ እያስከተለበት ያለውን ግጥም እያሰበ ።

ከቀረበለት ምግብ ምንም ሳያስተርፍ ጥርግ ማድረጉን የተመለከቱት’ትየ ወርቄ እየተቆናጠሩ ሳህኑን አንስተው ወደ ጓዳ ገቡ ።…

“አንተ ፣ ምን የሚሉት ትምባሆ ነው ደግሞ የዛሬው?” አፋቸውንና አፍንጫቸውን በግራ እጃቸው አፍነው ጠየቁት።

“እ… ያው የወትሮው ነዋ!”

አቋረጡትና “ትምባሆውን ራስህ ነህ የምትሠራው ልበል? ምናለ እንደሰዎቹ ጥሩውን አይተህ ብትገዛ!?”

“ገንዘብ ያስፈልጋል!… እ… ዋጋው ይለያይል …”

አላቸው ጢሱን እፍ እያለ ።

"ማን ግድ አለህ!ለአትተወውም?"

"ሲጋራ ከመተው ምግብ መተው ይሻላል!"

"ለነገሩማ የቄስ ልጅ ነበርኩ ትል የለም? ሃጢያት ነው!"

"ጓደኛ ነዋ! ጓደኛ አበላሸኝ ።… ገና አዲስ አበባ እንደገባንና አሜሪካን ግቢ እንደሠፈርን እ…ራብ ያስታማ ሳል እየተባለ… ለመድነው!"

ሰዓቱን በድጋሚ ተመለከተ ። አሁንም ስድስት ተኩል! ሰዓቱ መቆሟ ስለገባው በድንጋጤ ፊቱ ባንዴ ልውጥውጥ አለ ። ወደ ሥራው ከማንም በፊት ቀድሞ መግባት ነበረበት ።…

በፍጥነት እየተራመደ መስሪያ ቤቱ ሲደርስ ሰባት ከሩብ ሆኗል ። ደግነቱ ከሚቀልዱበት ባልደረባዎቹ ማንም አላጋጠመውም ። ቀድመውት ገብተዋል ። ከአንድ የፈረንጅ ቡችላ ጋር እየተዛለሉ የሚያውካኩት ዘበኞች ብቻ ነበሩ ።

ስምንት ሰዓት ላይ በአዲስ ካኪ ሳሪያን ኮትና ሱሪ የተለበጠ ተላላኪ አንድ ወረቀት ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠለት ። ወረቀቱ የያዘው መልዕክት "የአስተዳደር መምሪያ ባልደረባ የሆኑት ወይዘሪት ሶፊያ በዝውውር ወደ አሰብ ስለሚሄዱ ለመሸኛ ግብዣ የተቻላችሁን ያክል ፈርሙ!" የሚል ነበር ። አሥር የሚሆኑ ሠራተኞች ከስማቸው ፊት ለፊት የገንዘብ መጠንና ፊርማቸውን አስፍረዋል ። ሰላሳ… ሃያ… አሥራ አምስት… አሥር ፥ … ስምንት…፥…

እዚያ ላይ ከፍያለው በጣም ጨነቀው ። ለእስከዛሬው



ግድ አልነበረውም ። የመዋጮ መፈረሚያ ወረቀት ከቢሮ ቢሮ ሲዞር ውሎ እሱ ወደሚገኝበት መዝገብ ቤት መድረሱ የማይቀር ቢሆንም አንድ ግዜ ብቻ አዲሱን የአስተዳደር መምሪያ ሃላፊ አቶ ስመኝን ለመቀበል ለተደረገ ግብዣ አንድ ብር ፈርሟል ። ሌላ የሚያስታውሰው የለም ።

የአሁኑ አሳሰበው ። ሶፊያን በጣም ይወዳታል ። እንደሌሎቹ አትዘልፈውም ። አትቀልድበትም ። ብትስማ እንኳ በቀልዱ እጇን አታስገባም ። መግቢያ ፥ መውጫያ በሮች ላይ እንዲሁም በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲገናኙ ሰላምታ ታቀርብለታለች ፤ 'ጋሼ ከፍያለው…' እያለች ። ከዚህም ሌላ በብርድ በሽታ ታሞ በነበረበት ግዜ ሃያ ብር ሰጥታዋለች ። ስለዚህ ውለታ አለበት ። በሶፊያ የመሸኛ ግብዣ ላይ የተቻለውን ያክል አለመፈረምና በሌላ ግዜ እንደሚያደርገው ከግብዣው ቢቀር ውለታ — ቢስነት መስሎ ታየው ።

"ፈጠን በል እንጂ! ሃውልት'ኮ አይደለሁም!" ሲል ቁልቁል የሚመለከተው ተላላኪ አፈጠጠበት ።

"ይቅርታ ወንድሜ!እ… ሰዎች ስንባል ማሰብ አለብን። እ…"

"እፋ!" ተላላኪው የተሰላቸ መሰለ ።

"ብዙ የቆምክ አይመስለኝም ። እ… አትቸኩል ። እ…" ማጅራቱን እየፈተገ አንድ ብር ከሃምሣ መዘገበና ፈረመ ።

ተላላኪው የመጣበትን ሣቅ ለመመለስ አፉን በእጁ አድርጐ ፥ ወረቀቱን ይዞ ወጣ ።

የግብዣውን ዕለት ላለመርሳት በቁራጭ ወረቀት 'ሰኔ—

2’ብሎ ፃፈና ግድግዳው ላይ ለጠፈው ። ሁለት ቀን ብቻ ነበር የቀረው ።

ለግብዣው ዕለት ለእንደሱ ዓይነት ድሃ የአለባበስ ጉዳይ ትልቅ ፈተና መሆኑን ያውቃል ። አሁን የቸገረው የልብስ ጉዳይ አልነበረም ። ያለውን ያጥበዋል ። አብዛኞቹ ልብሶቹ ላዩ ላይ ያለቁ ቢሆኑም አማራጭ አልነበረውም ። አዲስ ልብስ ለመግዛት አቅም የለውም ። ለልብስ መግዣ ልበደር ቢልም ፡ ዕዳውን ከፍሎ ለመጨረስ ዓመታት ያስፈልጉት ይሆናል ። በዚያ ላይ የሶስት ወር የቤት ኪራይ ’ትየ ወርቄ ይጠብቁበታል ።

የቸገረው የጫማ ጉዳይ ነበር ። የእስከዛሬው ጫማው ባለመስኮቱ የጐማ ጫማ ነው ። አልሳካለት ብሎት እንጂ ሊቀይረው ካሰበ ብዙ ጊዜ ሆኖታል ። በዚህ ጫማ በርካታ ፌዞች ደርሰውበታል ። ሌላ ቀርቶ ፡ ‘ሀጋዊ–ወያኔ’ ተብሎበታል ።

ከሥራ ባልደረቦቹ ብድር እንዳይጠይቅ ፡ ሲያገኙት ከማፌዝ አልፈው ለሱ ችግር ደንታ እንደሌላቸው ያውቃል ። የመስሪያ ቤቱ የቁጠባና የብድር ማህበር ታወሰው ። የማህበሩ አባልና መስራችም ነው ። ግን የማህበሩ ፀሃፊ ወንድይራድ በሱ ላይ ከሚያፌዙት አንዱና ዋነኛው በመሆኑ ሊያነጋግረው አልፈለገም ።

አውጥቶ፡ አውርዶ አማራጮቹን ሁሉ ወረቀት ላይ ካሠፈረ በኋላ በምክንያት እያስደገፈ፡ አማራጭ ሊሆኑ የማይችሉትን ሰረዛቸው። የሚያዋጣው የቁጠባና የብድሩ ማህበር ብቻ መሆኑን ወሰነና አንድ በቅጡ ያልተፃፈ ማመል



ከቻ ይዞ ወደ ቢሮ ቁጥር 128 ሄደ። የቢሮውን በር አንኳኩቶ ሲገባ ፡ የማህበሩ ፀሐፊ ውንድይራድ አንድ የውጭ መጽሔት እያገላበጠና ሲጋራ እያቦነነ አገኘው።

ወንድይራድ ከፍያለውን እንዳየ፡ ለፌዝ በቋመጠ አቀራረብ ከተቀመጠበት ተሽከርካሪ ወንበር ብድግ ብሎ ተቀበለው። ጠረጴዛው ላይ የነበሩትን መፃህፍት፡ ወረቀቶች፡ …ወደ ግራ ወደ ቀኝ እየገፋ መልክ ካስያዘ በኋላ “ሻይ ወይስ ቡና?” አለው፡ አሊቃው እንደመጣበት ሁሉ።

ከፍያለው ምንም መልስ ሳይሰጥ ወንበር ስቦ ተቀመጠና ማመልከቻውን ሰጠው።

“ምን ችግር ገጥሞህ ነው?” አለው ወንድይራድ።

“ችግሩ የግሌ ነው። ስለእግዜር ብለህ ብድር ብትፈቅድልኝ። እ… የመቶ ብር ብድር…ሁለተኛ አላስቸግርም። እ…የማህበሩ አባል ነኝ። እ…” እጆቹን እያወናጨፈ ለማስረዳት ሞከረ።

“ዴክ ልትገዛ ነው ? ቪዲዮ እያሳየህ ከመንደር ልጆች ገንዘብ ልትገፍ ! ሃሃሃሃ … ! የታንጎ ሙዚቃና ቪዲዮ መደብር ቋሚ የቪዲዮ ካሴት ደምበኛ ለመሆን እንዳቀድክ ሰምቻለሁ። ግን ለምን የመዝገብ ቤት ትምህርት ተቋም አትከፍትም? ሌክቸረር ትሆናለህ። … ” የመጨረሻው የውስጥ ጥርሱ እስኪታይ ድረስ ሣቁን ለቀቀው፡ ሃሃሃሃ…!

“ስለእግዜር ብለህ !መቶ ብር ብቻ …የማህበሩ መስ

ራች ነኝ።እ…አንተ እንኳ ከመጣህ ሶስት ዓመትህ ነው። እ…እና ባክህ …”ማጅራቱን ጾከከ።

“ሂሳብ እያደረግን ስለሆነ ካለፈው ሰኞ ጀምረን ብድር ከልክለናል። እና አይቻልም” በማለት ወሽመጡን ቆረጠበት፡ የማገውን ጢስ እና እፍ እያለበትና መተርኮሻው ላይ እያወደመ።

የወንድይራድ የሲጋራ ጢስ፡ ሱሱን ቀሰቀሰበትና ከፍ ያለው ከውስጥ ኪሱ ግስላ ሲጋራ አወጣ።

”እ!እ!… እሱን ተወው…! እስም ስላለብኝ ነው” አለና ወንድይራድ አንድ ሮዝማን ሲጋራ ከፓኬቱ አውጥቶ እጁን ዘረጋለት።

“እግዜር ይስጥልኝ! ስወጣ የራሴን እጨሳለሁ። እና የብድሩ ጉዳይ…እ…”

“እሱንማ ነገርኩህ! በቃ።”

“ባስቀይምህ ይቅርታ አድርግልኝና ትላንት ወዲያ ለአቶ ስብሃት?….ማለቴ ለጓድ ስብሃት ፈቅዳችኋል። እ…”

“ያማ ስፔሻል ኬዝ ነው!”

“ምን አልከኝ?”

“ስፔሻል ማነስ ‘ልዩ’ ልዩ ችግር..!”

“ልዩ ችግር? አየህ ወንድይራድ!” ተነስቶ ቆመ። “ችግር ለተሸከመው ሁሉ ያው ችግር ነው። እ…የችግር ልዩ የለውም። እ…አጣዳፊ ችግር፡ ቀላል ችግር ሊኖር ይችላል። ግን ለሁሉም ችግር፡ ችግር ነው። ደግሞ እ…”



ወንድይራድ አቋረጠውና “ችግርን በተመለከተ አንድ ሪሰርች አቅርበህ ማሳተም ነው። ሃ…ሃ….ሃ…!ይቺን ካደርግ ሽማ ከፌ! የጠቅላይ ሚኒስትርነት…ቢያንስ ደግሞ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትርነትሽን ቀጨም አደረግሽ ማለት ነው ። ሃ…ሃ…ሃ…!”

እምባ የተናነቀው ከፍያለው “ ከማህበሩ አባልነት ሰርዙኝና ያዋጣሁት ይመለስልኝ። እ…ችግር ነው። ምን ይደረግ? ” አለ።

“ከመስከረም ሁለት በኋላ ጠይቀን” አለው ሌላ ሮዝማን ሲጋራ እየለኮሰ።…

ከፍያለው ንዴትና ብስጭት እየተሰማው፡ እምባ እየተናነቀው በመጣበት እግሩ ተመልሶ ወጣና ወደ ሚኒስትሩ ቢሮ ሄደ።

ሚኒስትሩን ለማግኘት እንደሚፈልግ የፅህፈት መኪና ታቅፋ ሹራብ የምትሠራውን ፀሐፊ ቢጠይቃትም “ስብበባ ይዘዋል !” በማለት እንቅፋት ሆነችበት ። ሚኒስትሩ ግን ስብሰባ ላይ አልነበሩም ።

ግማሽ ሰዓት ያክል ጠበቀ።…

“እባክሽ ንገሪልኝ! ሰዎች መረዳዳት አለብን! …እ…” አላት እያስተዛዘነ።

“ኤጭ!” አለችና ፀሃፊዋ የስልኩን እጀታ አንስታ ቁጥሮችን ጠቅ ጠቅ አደረገች። ጥቂት ከተነጋገረች በኋላ

"ግባ!" አለችው።

የሚኒስትሩን ቢሮ በር ከፍቶ ሲገባ ሆዱን ባር ባር አለው። ቤተኛ —አዳሪ ቤት የገባ ጀማሪ ጎረምሳ ይመስል ፍርሃት ወረረው። የሚኒስትሩ ቢሮ ውበትና ወለሉ ላይ የተነጠፈው ቀይ የፋርስ ምንጣፍ፣ እንዲሁም የሚያብረቀርቀው ጠረጴዛና የሚኒስትሩ የተቆጣ ፊት፣ ይህ ሁሉ ተዳምሮ ፀፀት አሳደረበት። "በቀረብኝ!" አለ በሆዱ።

"ጌታየ እኔ እ…ችግር አለብኝ። እ…የቁጠባና የብድር ማህበሩን እ … ብድር ጠየቅኩ ። እ … ግን ጓድ ወንድይራድ እ…" መንተባተቡ ጭራሹን ባሰበት ።

"ምንድነህ?" ብለው ሚኒስትሩ ድንገት ሲባርቁበት አንገቱን ደፋ።

"ጌታየ እኔ በዚህ መስሪያ ቤት እ…ለረዥም ዓመታት እ…በታማኝነት…"

"ውጣ ባክህ! ክሬዚ!… የብድር ይግባኝ ሰሚ መሰልኩት እንዴ ? …" አሉና ሚኒስትሩ በብስጭት ቡጢ ጨበጡበት ።

ከዓይኖቹ ፍልቅ ያለውን እምባ እየጠረገ ተመልሶ ወጣ።

ሌላ አማራጭ ብልጭ አለለት። በአስተዳደራዊ ሥራ አንጋፋነታቸው፡ ባለጉዳይን አዝናንተው ችግሩን አድምጠው ፡ ከቻሉ ችግሩን ፈተው ፡ ካልቻሉ ችግሩ የሚፈታበትን መንገድ ጠቁመው በማስተናገድ የሚታወቁት የአስተዳደር



መምሪያው ሃላፊ አቶ ስመኝ፡ ከፍያለውን ፈገግ ብለው ነበር የተቀበሉት። ፈገግታ አይለያቸውም።

"አቶ ከፍያለው! ዛሬ ምን እግር ጣለህ?" አሉት እንዲቀመጥ ባዶ ወንበር እያመለከቱት ።

አንገቱን ቁልቁል አጥፎ ዝም።

"በል እንጂ!" አሁንም ፈገግ እያሉ ።

ከነተበው ነፍስ—ይማር ኮቱ የውስጥ ኪስ ለወንድይራድ ሰጥቶት የነበረውን ማመልከቻ አውጥቶ አቀበላቸው።

ማመልከቻውን እያነበቡ፡ ጭንቅላታቸውን ግራ ቀኝ እያወዛወዙ፣ ከንፈራቸውን መጠጡና "ከዚያስ?" አሉት።

ትከሻውን ሽቅብ መታ።

ማስታወሻቸውን ገልጠው ከፃፉ በኋላ አንድ ባለ ሃምሳ ብር ኖት ከመሳቢያቸው አውጥተው ሰጡት። ጉልበታቸውን ሊስም አጎንብሶ ሲጠጋቸውም "አይገባም! ነውር ነው!" ብለው ከለከሉት።…

ምሽት ላይ ከፍያለው በእድሳት የተቃና አሮጌ ቆዳ ጫማ በአሥራ ሁለት ብር ገዝቶ ወደ ቤቱ ገባና እግሮቹን አጥቦ ካደራረቀ በኋላ ለካው። ወዲያና ወዲህ እያለ ሞከረው። የጫማውን ጫፍ በጣቶቹ እየነካካ፣ ያረጀውን የጣውላ ወለል እየተመተመ ፈገግ አለ።

"ጫማ ገዛህ እንዴ ?" አሉት 'ትዬ ወርቂ ማማሰያቸውን ከሚንተከተከው ዶኬ አውጥተው መዳፋቸውን በማስነካት እየቀመሱ ።

"ከመስሪያ ቤት ነው የተሰጠን። እ…ለሁላችን/!" ፈገግ እያለ። ለ'ትየ ወርቄ ያዘጋጃት መልስ ነበረች። ይህቺ ውሸት ምናልባት በህይወቱ የመጀመሪያ ልትሆን ትችላለች።

"ወታደር መሆንህ ነው ? ወሽካታ ! ቢሻው ቀበሌ ፣ ቢሻው ማዘጋጃ ቤት ይስጥህ። እኔ የምፈልገው ገንዘቤን ነው። ገንዘቤን ጠብ አድርግ! አለበለዚያ ጉድ ይፈላል።"

ሰሞኑን አንድ የቀበሌ ጥበቃ—ጓድ በውሸማነት ስለያዛቸው የተጣሉትን ሁሉ 'ጉድ ይፈላል!' ማለት ጀምረዋል። ከፍያለውም ምን ማለታቸው እንደሆነ ገብቶታል።

"ነግሬሃለሁ! ኋላ እንዳታዝንብኝ" አሉትና እንደ ሀረር ሰንጋ የሚያረግደው ዳሌያቸውን እያወዛወዙ ወጡ።…
እሁድ በማለዳ ከመኝታው ተነስቶ ቀጨኔ መድሃኔዓለም ቤተክርስትያንን ተሳልሞ ከተመለሰ በኋላ አዲሱ ጫማውንና ቀዳዳዎቹ ተጠግነው፣ ታጥፎ የተተኮሰ ሱሪውን አጠለቀ። ሱሪው ትንሽ ቢያጥረውም አዲሱ ጫማውን በደንብ የሚያሳይለት በመሆኑ አልከፋውም።

አንድ የተበጣጠሰ ካናቴራ ለብሶ፣ በላዩ ላይ የመጀመሪያ ቀለማቸውን ለመለየት አዳጋች የሆኑ ሁለት ሸሚዞችን ደረበ። ታጥቦ፣ ተተኩሶ፣ በጋዜጣ ተጠቅልሎ ከተቀመጠ ስድስት ወር የሚደፍነውን ጥቁር ነፍስ— ይማር ኮት ከትልቁ ካርቶን አውጥቶ ለበሰና የሠፈሩ የዕድር ዳኛ የሰጡትን የፍየል ምላስ የምታክል ዝንጉርጉር ክራቫት በአንገቱ አጠለቃት።



በተሰነጣጠቀችው መስተዋት ራሱን ሲያይ ከልቡ ሳቀ። የኋላውንም፣ የፊቱንም እየተሿሿረ ካስተዋለ በኋላ፣ በራጭንቅላቱ ላይ አልፎ አልፎ የበቀሉትን ፀጉሮቹን ወደኋላ አስተኛቸው።

በህይወቱ እንደዚህ ሽክ ብሎ አያውቅም። በዚያ ቀንም የ'ትየ ወርቄ ቂጣና ያልፈላ ዶኬ አላስኘውም።

በአዲሱ ተረከዛማ ጫማው አሮጌውን የጣውላ ወለል እያንሳጠጠ ሲወጣ "ምሣ አትበላም እንዴ ?" አሉት አለባበሱን እያስተዋሉና የሽሙጥ እያዩት።

"ዛሬ ምሣ አልበላም። ምክንያቱም እ…"

"ታዲያ ማን ሊበላልህ ነው? የማትበላ ከሆነ ለምን አሰራኸኝ?"

"እንዴት መሰለዎት'ትየ ወርቄ ! ዛሬ ግብዣ ስላለ …"

"ድንቄም!" አሉና ቀጭን የሽሙጥ ሣቅ ስቀው "አንተም ተጋበዝክ? አልበላም ካልክ እኔ ድሃዋ አልከስርም። ሂሳቤን ትመዘግባለህ። አለበለዚያ ዋ!"

እሱም ምልልስ አልፈለገም። መዝግቦላቸው ወደ ግብዣው ቦታ ሄደ። ግብዣው ቅድስት ማርያም ጀርባ ከሚገኘው ትልቅ ግቢ ነበር። በሶፊያ ቤት።

የቤቱ ትልቅነትና ዘመናዊነት ፣ የግቢው ማማር አስደነገጠው። የድግሱን ሁኔታ ማመን አቃተው። ካሰበው በላይ ሆነበት። እሱ የሚያውቀው ድግስ፣ ማህበር፣ ዝክር፣ ፍታት፣ ክርስትና፣ …በእነዚህ ላይ ደግሞ ሁለት ወይም ሶስት ዓይነት

ወጥ ቀምሶ፣ ሶስት ብርጭቆ ያክል ጠላ አጋብቶ ከመመለስ ውጪ የሞቀና የደመቀ ሁኔታ ገጥሞት አያውቅም።

የሙዚቃው ጩኸት፣ የአስተናጋጆች ሽርጉድና ቅጥየለሽ ውካታ፣የቢራ ጠርሙሱ ኳኳታ፣ የሲጋራው ጢስ ትንፋግ፣ የምግቡ ሽታ… ሁሉ ለጉድ ነው።

ከፍ ያለው አንድ ወንበር ስቦ ተቀመጠና ዙሪያ ገባውን አማተረ። አስተናጋጆቹ ያመጡለትን ምግብ ጥርግ አድርጎ ከበላ በኋላ፣ በሁለት ሰዎች ግራና ቀኝ ተይዞ ከሚዞረው የቢራ ሣጥን ላይ አንድ ጠርሙስ አንስቶ አስከፈተና ተጎነጨ። ግስላ ሲጋራውን አውጥቶ ለኮሰ። አንዴ ማግ አድርጎ፣ ጢሱን በአፍንጫውና በአፉ ሲያወጣ አጠገቡ የነበረው ወጣት የቢራ ጠርሙሱን አንጠልጥሎ ከፍያለውን እየገላመጠ ፊት ለፊት ከነበሩት ሴቶች ጋር ተቀላቀለ።…

ግብግቡው መልኩን እየቀየረ መምጣት ጀመረ። ትርምስ በዛ። አሥር የሚሆኑ ወንዶችና ሴቶች የቢራ ጠርሙሳቸውን እንደያዙ፣ ከመጠን በላይ በሚጮኸው የፈረንጅ ሙዚቃ መውረግረግ ጀመሩ። ከፍያለው አፉን ከፍቶ ይመለከታቸዋል። በተለይም የሴቶቹ እንደዚያ መሆን አላስደሰተወም።…

ደንገዝገዝ ማለት ሲጀምር ተስተናጋጁ ሁሉ ለየለት። አፍ ለአፍ ገጥሞ የሚያወራው ፤ ቀሚስ ገልቦ ጭን የሚያሸው፣ ከንፈር ለከንፈር ገጥመው የሚሳሳሙትን፣ ተቃቅፈው በሰመመን እንደ ቅቤ የሚቀልጡትን ሲያይ ላብ ላብ አለው። የጠጣው አራት ጠርሙስ ቢራም ናላውን አዞረው። አቅለሸለ



ሸው። ሞቅ እያለው በሄደ ቁጥር ምክንያቱን ሳያውቀው ነገር ነገር አለው።

በመካከሉ "ሃሎ ሌዲስ ኤንድ ጄንትልሜን! ሃሎ ሌዲስ ኤንድ ጄንትልሜን!" የሚል ድምፅ በጭብጨባ ታጅቦ ሲያስተጋባ ሁሉም ፀጥ አለ። የቆመው እንደቆመ፣ የተቀመጠው በተቀመጠበት ሆኖ ወደሚያጨበጭበው ወጣት አፈጠጠ ።

"ሰላም ለሁላችን ! ተዝናኑ ተጫወቱ ! ኢንጆይ ዩር ሰልቭስ! ወይዘሪት ሶፊያ ሁለተ ጠርሙስ ስኮች ውስኪ ጀባ ስትለን አምስት ባልደረቦቿ ደግሞ አምስት ጠርሙስ ቲቸርስ ዊስኪ አቅርበዋል። ኦሽር ናይት ነው ዳንሱ!እኬ! …"

ንግግሩን ሳይጨርስ ተስተናጋጁ ጭብጨባውን አቀለጠው ። ፀጥ ብሎ የነበረው ሙዚቃ ወደነበረበት ተመለሰ ። …

ከፍያለው ግን ብዥ ብዥ አለበት። የሆነ ስሜት መንፈሱን አወከው ። መላው ተስተናጋጅ ፀጥ ብሎ እንዲያደምጥ በማድረግ "አሁን እኔ ወንድማችሁ አይደለሁም?" ሊል ፈለገ። ምን እንደገፋፋው አያውቅም።

ለዚሁ ዓላማ ከወንበሩ ለመነሣት ሲሞክር ተንገዳገደና ተመልሶ ዘጭ አለ። የሚያየው ነገር ሁሉ ህልም መሰለው። 'መሬት ትዞራለች የሚባለው ሃቅ ነው' አለ ፤ በልቡ ።

ያለ የሌለ ሃይሉን አሟጦ ተነሳና እየተንገዳገደ ወደ ሽንት ቤት ሲሄድ “አሲስታንት ፕሮፌሰር ከፍያለው ደመና…ጄኔራል ዳይሬክተር ኦቭ ኢትዮፒያን…” አለው ወንድይራድ፤ በተሳሰረ አንደበት። እዚያ የነበረ ሁሉ ሣቀ። ወንድይራድ ለማለት የፈለገውን በሳቅ አቋረጠው።

በቦዙ ዓይኖቹና በአፍንጫው እየተመራ ወደ ሽንት ቤት ሲሮጥ በገጠመው ነገር አፉን ከፍቶ ቀረ። ያየውን ማመን አቃተው። ከመስሪያ ቤቱ ባልደረቦች ጌድዎንና ማርታ ጨለማን ተገን አድርገው መርፌና ክር ሆነዋል።

“በስመአብ ወልድ !” የሚል ቃል አመለጠው። በድንጋጤ ስካሩ ለቀቀው። በቀጥታ ግቢውን ለቆ ወጣ።

የቀጨኔ መንገድ ጭር ብሏል። አልፎ አልፎ ብቻ መኪናዎች ሽር እያሉ ያልፋሉ። ከዚያ ውጪ የሚንቀሳቀስ ነገር አይታይም።

ዋናውን መንገድ እየለቀቀ ፣ ወደ ቤቱ የሚያደርሰውን ኮረኮንቻማ መንገድ ሲያያዝ ፍርሃት በመላ አካላቱ ተሰራጨበትና የሚረግጠውን ሳያስተውል ሩጫ ጀመረ። ግራና ቀኝ፣ ፊትና ኋላ እየተገላመጠ መንገዱን ቀጠለ። እህል ውሃ የሚያሰኝ ድንጋይ አንስቶ ዙሪያ ገባውን እየቃኘ ቢገሠግሥም ልቡ ድው ድው እያለች ፈርታ ታስፈራዋለች።

ድልድዩን እንደተሻገረ አንዳች ነገር ማጅራቱ ላይ አረፈበት። ከዚያ በኋላ ትንፋሹ አጠረ። የልቡ ምትም ቀነሰ።…



ለምን ያህል ግዜ እንዲያ ሆኖ እንደቆየ ባይታወቀውም ዓይኖቹን ገልጦ አካባቢውን ሲቃኝ ያለበትን ማወቅ ተሳነው ። ጥቅጥቅ ጨለማ ከቦታል። የነፍሳት ሲርሲርታ ይሰማል። የጅብ ጩኸት አካባቢውን ያምሰዋል።

በዚህ ጥቅጥቅ ጨለማ አፍጦ ዙሪያውን ቃኘ ። አካላቱን ቢዳስስ ልብሱ በሙሉ ተወስዷል። የቀረው ቢኖር የታጠቀው አሮጌ የውስጥ ሱሪው፣ የተቦጫጨቀ ካኒተራውና አንድ ሸሚዝ ብቻ ነበር። ሃያ ብር ገደማ ያስቀመጠበት ጥቁሩ ነፍስ ይማር ኮቱ፣ ሮመር ሰዓቱ፣ ጫማው…ሁሉም የሉም። መነፅሩን እንኳ አላስቀሩለትም።

እየተንገዳገደ ቤቱ ደርሶ በዝግታ ጓዳውን ከፍቶ ገባ። ‘ትየ ወርቄ ተኝተዋል። የጠፍር አልጋው ላይ በደረቱ ድፍት አለ።

በማግሥቱ ሥራ አልገባም። ፈቃድም አልጠየቀም። መጥቶ የጠየቀውም አልነበረም ፣ ከ‘ትየ ወርቄ በቀር ፣ ለዚያውም ለሂሣባቸው ሲሉ።

የጠፍር አልጋው ላይ ተደፍቶ ውሎ ቀትር ላይ አይኖቹን ከፈት ሲያደርግ ጣንቲሞች የሚያጠራቅምባት ትንሿ ጣጥኑ ተሰባብራለች። በመኝታ ክፍሉ ውስጥ የነበረው ኮተቱ ሁሉ የለም። ‘ትየ ወርቄ እንደተካሱበት ለማወቅ ግዜ አልፈጀበትም። ደግነቱ አላባረሩትም። ትርፍራፊ ይጥሉለታል። ውሃ ያቀብሉታል።

ለሁለት ሣምንት ያክል ከማቀቀ በኋላ ፣ ከሙታን ሠፈር መቃብሩን ፈንቅሎ የወጣ ጣረሞት መስሎ በምርኩዝ እየተ

ረዳ ይሠራበት ወደነበረው መስሪያ ቤት ሊያዘግም ሞከረ። ግን ከአጭር ጉዞ በኋላ አቃተው። ሌላ የሚሄድበት ቦታም አልነበረውም። በአቅራቢያው ከሚገኝ አጥር ሥር ተቀመጠና እጆቹን ዘረጋ፡ ለልመና።

ሐምሌ 1981
ለመምህር አቢይ የሻነው
ጉድጉዳ

# ንቃት…ንቃቃት

ጭርምትምቱ በድንጋይ ተቃንቶ "ዘመናዊ ፀጉር አስተካካይ" የሚል ጽሑፍ ባልተመጣጠኑ ፊደላት የሰፈሩበት ቆርቆሮ የተንጠላጠለባት ፣ የማዘጋጃ ቤት ፕላን የማያውቃትና የሃብታም ቤት ግምብ ተንተርሳ የቆመች ዛኒጋባ ናት ። በፀሐይ መውጫ በኩል የቆመው የጭቃ ልስን ግድግዳዋ ለስሙ ያህል በስሱ ኖራ ሽው ያለበት ቢሆንም ፣ የተቀሩት ግድግዳዎች ምርጋቸው ረግፎ የሸረሪት ድር ለብሰዋል ።

ወደ ውስጧ ጐራ ሲባል ፣ ከጣራዋ አግዳሚና ወራጅ የተንዠረገገው ጥቅርሻ ያስፈራራል ። በእበት በተለሰነ የሸምበቆ ግድግዳ ተከፍላለች ። የመጀመሪያዋ ክፍል ባልቻ ፀጉር የሚያስተካክልባት ስትሆን ፣ ጓዳይቱ ደግሞ በትርኪ ምርኪ የተጨናነቀች ሆና ፣ አይን የሚገባ ነገር ቢታይባት ካሊም የተነጠፈባት የባልቻና የሚስቱ ፣ የአንጓች ፣ የጠፍር አልጋ ነው ።



የባልቻ ክፍል ፣ በእርሱ አባባል 'ቢሮው' ፣ በጋዜጦች የተለበጠች ስትሆን ፣ አልፎ አልፎ ከውጭ መፅሄቶች ላይ ያለምንም ጥንቃቄ የተገነጠሉ ስእሎች በአጋም እሾህ ተቸንክረውባታል ። በግራ በኩል አራት እግሮቹን ትናንሽ ጠፍጣፋ ድንጋዮች ላይ ያሳረፈና ፣ ለጥንቃቄ ያህል ፣ አንደኛው እግሩ ከሸምበቆው ግድግዳ ጋር በወፍራም ሲባጐ የተጠፈረ ሞላላ ጠረጴዛ አለ ። ሁለት የዛጉ የፀጉር መቀምቀሚያ መኪናዎች ፣ ጣት ማስገቢያቸው ላይ ጨርቅ የተጠመጠመባቸው ሶስት መቀሶችና ያገለገሉ በርካታ ምላጮች ተዝረክርከው ይገኙበታል ። በቆረቆንዳ የተወተፉ ስድስት ያህል ጠርሙሶችም ይታያሉ ። አንደኛው ውኃ ፣ ሁለተኛው አልኮል ፣ ሦስተኛው ባልቻ 'ኮሎኝ' ፣ የአገሬው ሰው ግን ሽቶ የሚለው ፈሳሽ ፣ አራተኛው ቀለሙ ከቀይ ወደ ቢጫ ፣ ወይም ከቢጫ ወደ ቀይ እየተለወጠ የሚሄድ ፣ ምስጢሩንም የሚያውቅ ባልቻ ብቻ ነው ፣ የፎረፎር መድኃኒት ይዟል ። የተቀሩት ሁለቱ ባዶ ናቸው ። ከጠረጴዛው ሥርም ካፍ እስተገደፉ የሞላ የፀጉር ማጠራቀሚያ ካርቶን አለ ። ይህ ሳይሆን አይቀርም ፣ ቤቱን አንዳንዴ ፣ በሚሰነፍጥ ሽታ የሚሞላው ።

ከጠርሙሶቹ ከፍ ብሎ ስንጥቅ የበዛበትና በፕላስተር የተጠጋገነ አንድ ገጣባ መስተዋት በፍየል ቀንዶች ተደግፎ ተሰቅሏል ። በየጊዜው የሚፀዳ ባለመሆኑም ቆሽሾ መልክ በውል አያሳይም ።

ሸንበቆ ግድግዳው ላይ ከተንጠለጠሉት ሁለት አዳፋ ፎጣዎችና አንድ የአንሶላ ትልታይ ግርጌ የፊሊፕስ ራዲዮ አለ ። ባልቻ ራዲዮውን በጣም ይወደዋል ። ተአምራዊ እቃ አድርጐ ነው የሚመለከተው ። ከምንም በላይ ይህን ራዲዮ

የሚወድበትም ምክንያት አለው ። ፀጉር አስተካካይ ከነበሩት ከአባቱ ከባሻ መኩሪያ በውርስ ያገኘው ከፍተኛው ሀብት ከመሆኑም በላይ ለሃያ ሁለት አመታት አብሮት ኖሯል ። የሚያሰራጨው ዜናና መልእክትም በስብእናው ላይ ትልቅ ተፅእኖ አሳድሮበታል ። ስለዚህ ካጠገቡ ሊያርቀው አይፈልግም ።

ነፍሳቸውን ይማረውና ፡ አባቱ ባሻ መኩሪያ ከራዲዮ የሚተላለፍ ዜና እንተርሰው የራሳቸውን ግምታዊ ትንታኔ በመስጠት ዝናን ያተረፉ ሰው ነበሩ ። እናም ባልቻ ይህንንም ዝና አብሮ ወርሷል ። አባቱ ሲሞቱ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ነበር ። ግን ምንም አማራጭ ስላልነበረው ወዲያው ትምህርቱን አቋርጦ በአባቱ እግር የፀጉር ማስተካከል ስራውን ጀመረ። እስከ አምስተኛ ክፍል መማሩም ያስገኘለትን እውቀት መሰረት አድርጐ ከራዲዮ የሚያገኘውን ዜና በማስመልከት በተለያዩ አገሮችና መንግስታት ላይ ትችት አሰጣጡ ከአባቱ አልቆታል ። በዚሁ ባህርይው "የመንግስት ተቃዋሚ!" ተብሎ በአንድ ወቅት ለሶስት ወራት ያህል ዘብጢያ ወርዶ ነበር ። 'ንቃት' አግኝቶ መውጣቱም ይበልጥ ፖለቲከኛ አድርጐት በጓደኞቹ ዘንድ የአለምን ውስብስብ ገፅታዎች አንጠርጥሮ እንደሚገነዘብ ውስጥ አዋቂ ተቆጥሮ አክብሮትንና አድናቆትን አትርፏል ።

ፀጉር ቤቱ እምብዛም ደምበኛ የላትም ። ከተማይቱ ከጊዜ ወደጊዜ ዘመናዊነትን እየተላበሰች በመጣች ቁጥር በሽርፍ ተራ እንደ አሸን የሚፈሉት የፀጉር ማስተካከያዎች ከደምበኞች እያራቆቱት ሄደዋል ። በቀን የሁለት ህፃናት ፀጉርና የሶስት ያህል ሽማግሌዎች ፂም ቢያስተካክልና ቢላጭ ነው ። በዚች ገቢው ጐጆውን ቀጥ አድርጐ መያዝ ባለመቻሉ



ውራጅ ልብሶች ፡ ያረጁ ራዲዮኖችና የተጠገኑ ሰአቶች ደላላ ሆኗል ። አንዳንዴም ፡ ትርፍ የጋራ ፡ የሎተሪ ቲኬቶች ከአዟሪዎች እየተቀበለ ከመስተዋቱ አጠገብ ሰቅሎ ይሸጣል።

ባልቻ ሲበዛ ወሬኛ ነው ። ወንበር ላይ ከተቀመጠው ተስተካካይ ጀርባ ተገትረው ነጠላ እየቋጩ ፡ ወይ መልካቸውን በመስተዋቱ ለማየት እየተንጠራሩ ፀጉራቸውን ከሚያበጥሩና ፂማቸውን ከሚከረክሙ ደላሎችና ስራፈት ጓደኞቹ ጋር በሚያደርገው ክርክር ይመሰጣል ። ላለመሸነፍ ሲልም በግራ እጁ የሚይዘውን ሚዶ ወደ ተሚጋቹ እየቀሰረ ፡ በቀኝ እጁ የሚይዘውን መቀስ በማንቀጫቀጭ ብቻ የሚያሳልፈው ጊዜ ይህ ነው አይባልም ።

በዚህ ሳቢያ ከበርካታ ደምበኞቹ ጋር ዱላ ተማዝዟል ። በክርክሩ ስለሚመስጥ ሳይታወቀው ጉንጭ የሚሸነትርበትም ጊዜ እንዳለ መወራቱና ባልታዘዘው ልክና መልክ እየሸለተ ማበሳጨቱ ለደምበኞቹ መራቅ ዋነኛ ምክንያቶች ሳይሆኑ አልቀሩም ።

ጓዳዋ ተከትታ እንካስላንትያውን ስታዳምጥ ከምትውለው ሚስቱ ጋርም ስምምነት የለውም ። በፖለቲካው ዳግመኛ ዘብጢያ እንዳይወርድባት ትሰጋለች ። ከስራ ፈቶች ጋር ከሚፈጥረው መቋጫ የሌለው ንትርክ ይልቅ በርትቶ እንዲሰራና ጐጆዋቸውን ለማሻሻል ጥረት እንዲያደርግ ትመክረዋለች ፡ ታስመክረዋለች ። እርሱ ግን ምክሯን መቀበል ቀርቶ ጭራሹን አያዳምጣትም ። እንዳውም ማይምነቷን እየጠቀሰ ያንቋሽሻታል ። የስድብ ናዳ ያወርድባታል ። ሞቅ ያለው ቀንም፣ ከራስጌው የማይለየውን የክትክታ በትር አንስቶ ይዠልጣታል ፡ ዳግምኛ እንዳይለምዳት እያስማላት ።

ለራዲዮው ባትሪ ድንጋይ የገዛበት ጊዜ ትዝ አይለውም። በአካባቢው የሚገኙ ባለሆቴሎችን በቋሚ ደምበኝነት ተጠግቶ ፡ አብቅቶላቸዋል የተባሉትንና ያገለገሉ ባትሪ ድንጋዮችን እየሰበሰበ በየጊዜው ለራዲዮው ያጐርሳል ።

ከአማርኛ ስርጭት ፡ የጀርመን ራዲዮ ጣቢያ ነፍሱ ነው ። የቢ·ቢ·ሲ·ንም የእንግሊዝኛ ፕሮግራም ይከታተላል ። ይህን እንኳ የሚያደርገው ሲቀብጥ እንጂ ፡ ቋንቋውን የማዳመጥ ችሎታ የለውም ፡ የከተሞችን ስሞች ለመያዝ ካልሆነ በቀር ። ዋናው ነገር ፡ ቤቱ ጭር አይልም ።

ባልቻ ስለአለም ፖለቲካ ጣጣ ዘወትር ይጨነቃል ። ያስባል ፡ ያሰላስላል ። ካልተባለ ነገር ተነስቶ እልህ እየተናነቀው የራሱን አስተያየት ይሰነዝራል ። የራሱን ውሳኔ ይሰጣል ። የአለም አስከፊና ዕልመታዊ ገፅታዎች እንጂ በጐና ብሩህ ጐኖች ፈጽሞ አይታዩትም ።

የድርቅ ኮሚሽን ኮሚሽነር ፡ ድርቁ በሰሜን ወሎ ስላስከተለው ችግር የሰጡትን ጋዜጣዊ መግለጫ ፡ ራሱ በሚያጠናቅረው ጥበብ አጣም የአሜሪካ መንግስት ለኢትዮጵያ መንግስት እርዳታ ለመስጠት መዘጋጀቱን ፡ ነገር ግን የሩሲያ መንግስት ያን እደተቃወመና እህል በገፍ መጫን እንደጀመረ ከጀርመን ራዲዮ ጣቢያ የሰማ መሆኑን ያወራል ። ይተነትናል ። የታንዛኒያው መሪ ለጐብኝት ወደ ኢትዮጵያ የመምጣታቸውን ዜና ከሰማ ፡ ያን አስታኮ ስለሶሻሊዝምና ስለኢምፔሪያሊዝም ፍጥጫ በስፋት ይዘረዝራል ። ሶስተኛው የአለም ጦርነት የመቃረቡን መርዶ ያስከትልና ስለ 'ስምንተኛው ሺህ' መዳረስ አንድ አስደንጋጭ ስዕል ያስቀምጣል ። በህንድ አገር አደገኛ ጐርፍ በርካታ ሰዎችን ቢገድልና ንብረት ቢያወድም የአሜሪካ መንግስት የሚፈጽመው ደባ



መሆኑን አይኑን ሳያሽ ይናገራል ። ኢጣልያ ለኢትዮጵያ የምግብና የመድሀኒት እርዳታ መስጠቷን ቢሰማ ፡ የአድዋና የማይጨው ጦርነቶች ያስከተሉባትን ሽንፈት ለመበቀል በእርዳታ ሳቢያ ኢትዮጵያን ልታጠቃ እንደተዘጋጀች አድርጐ ያቀርበዋል ።...

እለቱ ዘመን መለወጫ ነው ። የከተማው ሰው እንደየአቅሙ በአሉን ለማክበር ተፍ ተፍ ይላል ። የዛኒጋባው አዋሳኝ አቶ ደርቤ በጠብደል ኩሊ አሸከመው ያመጡትን ሙክት ጥለው ብልት ያወራርዳሉ ። አበባ የሚመስሉት ልጆቻቸው ባማሩ ልብሶች ተሽቆጥቁጠዋል ። በራየ የሀገር ባህል ቀሚስ የተሽሞነሞኑተ ሞንዳላ ባለቤታቸው እመቱ አበዘነትም በኩራት ተንጠርበው ገባ ወጣ ይላሉ ።

ባልቻም እንዳቅሙ መናኛ ብጤ ፡ ግን አዲስ ካኪ ሱሪ ፡ አጥፈ.ቋል ። እንጓችም ብትሆን ፡ ወጉ አይቅርብኝ ነውና ፡ አቻምና ለጥምቀት ገዝታው ጭንቅ ካልሆነባት በቀር ከሰንዱቅ የማታወጣውን የከት ባለአበባ ቀሚሷን ሳብሰብ አድርጋ ለብሳ ጓዳዋ ትርመጠመጣለች ።

ፊቷ በቅሬታ ስሜት ጠውልጓል ። በልጅነት ዕድሜዋ ፡ በዘመን መለወጫ በአል እለት የነበራት የገጠር ህይወቷ ድቅን እያለባት ትተክዛለች ።

"ገንዘብ ካለህ ስጠኝ" አለችው ፡ ስትፈራ ስትቸር ።

"ለምን?" አላት ባልቻ ።

"ጠላ መግዣ ።" እፍ እፍ እየተባለ የሚሳብ ጉሽ ጠላ በአይኗ ይዞራል ።

"የለኝም ።"

በእርግጥም የዛንለት ገንዘብ አልነበረውም ። በሌለው እለት ደግሞ ኩርፊያ ኩርፊያ ይለዋል ። ስድብና ግልምጫ

ይቀናዋል ።

ትንሽ ቆያይታ "ቅቤው እማያሰማ ብጤ ነው ። ዘይት ጠብ እንዳደርግበት ሳንቲም ስጠኝ" አለችው ።

"ከየት ላምጣ?" ሲል አፈጠጠባት ።

"ትናንት ማታ ከምታጨበጭብበት ..." ብላ የጀመረ ችውን ባልቻ አላስጨረሳትም ።

"በሽታ ይጨባብጥሽ! እንግዲህ ባመት ባል ቀን በጠዋት አትነትርኪኝ" ሲል ደንፍቶባት ብድግ አለ ።

ማታ በእርግጥ ኪሱን አራግፎ ሞቅ ብሎት ነበር የገባው ። ግን አንጓች አንድ ፡ ሁለት ብር አያጣም የሚል ተስፋ ነበራት።

ብድር እንዲፈልግም ጠይቃው ነበር ። "ብድር ለማ ንም አልበጀ ። ከተባበሩት መንግስታት የሚበደረውን እንኳ አሜሪካን እያስጨነቀው ነው" በሚል ትምህርት አፏን እንድትዘጋ አደረጋት ።

"በል ፡ ዶሮውን እረድልኝ" አለችው ፡ በታሰሩ እግሮቹ እንጣጥ እንጣጥ እያለ ጣሳ ውሀ ደፍቶ ፡ ጀበና ገልብጦ ፡ ስኒ ከተኮለኮለበት ረከቦት ላይ ሲያርፍ ቀልቧን የገፈፈውን አመለኛ አውራ ዶሮ እየረገመች ።

ባልቻ ዶሮውን በአሮጌ ቢላዋ እየገዘገዘ "በግ ቢሆን ኖሮ ቆዳው ተሽጦ ስንት ቀዳዳ በደፈነ" አለ ። የተናገረው ለራሱ ነበር ።

"ለቆሌው ያሀል ፡ ደም ካየን ይበቃናል" አለች አንጓች ። ባልቻ ያዳመጣት አይመስልም ። ራዲዮኑን ከራስጌያቸው አነሳና መጎራጎር ጀመረ ።

ሁለት የሰፈር ልጆች የእንቁጣጣሽ ስዕሎችን ይዘው ገርበብ ያለውን የፀጉር ቤት ገፍተው ገቡ ፡ "አባ ባልቻ! አባ



ባልቻ!" እያሉ ።

ባልቻ ብርድ ልብሱን ተከናንቦ ተኛ ።

"የእንኳን አደረሳችሁ ነው?" ስትል አንጓች ስሜቷን ደብቃ ሁለቱንም ሳመቻቸው ። እነርሱም እየተቅለሰለሱ በእርሳስከተሳሉ ወረቀቶቻቸው መሀል አንዳንዱን እየመዘዙ ዘረጉላት ።

"ያሳድጋችሁ!" በማለት አንዱን ብቻ ተቀበለቻቸውና "ይህን ደግሞ ለሌላ ሰው ስጡ ። እንዳያልቅባችሁ ። ኋላ ብር መንዝሬ እሰጣችኋለሁ ፤ እሺ? ... ጐበዞች!" በማለት ሸኘለቻቸው ።

ልጆቹ ወንድምና እህት ስለሆኑ ፣ አንጓች አንዱን ወረቀት ብቻ መቀበሏን እንደሁነኛ አማራጭ ወስዳዋለች ። እነርሱም አልተሻሙም ።

"ኋላ እንምጣ?" አላት ወንዱ ። የሚፈልጋትን አስር ሳንቲም እጅ በእጅ ባለማግኘቱ ቅር የተሰኘ ይመስላል ።

"አዎ ፡ በኋላ ና!"

ልጆቹ ከወጡለት በኋላ ባልቻ የተከናነበውን ብርድ ልብስ ወረወረና ተነሳ ። "ቁርስ የለም?" አላት ።

በገብስ እንጀራ ላይ ያደረ ሽሮ ወጥ ፈሰስ አድርጋ አቀረበችለት ።

"አንቺስ አትበይም?"

"በላሁ!"

"እሀል ሳትቀምሺ ይህን ባዶ ቡና መለጋት የልብ ሀመም ያመጣብሻል ። ኋላ የለሁበትም! የልብ ሀመም መድኃኒት እንኳን አገራችን እንግሊዝም አልሰራችም" አለና የጐረሰውን እስኪውጥ አቋረጠ ።

“ምናለ ይህን ንትርክህን ትተሽኝ ሳንቲም ብትሰ
ጠኝ?”

“ከየት ላምጣ ነው’ኮ እምልሽ! ሳንቲም የሚቀጠቅ
ጡት ጃፖኖች እንጂ እኔ መሰልኩሽ? ኑሮ እየተወደደ መ
ቷል ። የአለም ገበያ ይዋዥቃል ። ዳሩ አንቺ አለም ምን ሁኔታ
ላይ እንዳለች የት ታውቂና! ሽንኩርት … ዘይት… ትያለሽ።
አረብ ሴራ ጀምሯል ። ዘይት ውስጥ ምናምን እየጨመረ
እንዳይጨርሰን!… አንቺ አይገባሽ መቼስ!” እያለ አላምጠ
ሲወጥ ትን አለው ። “እስቲ ውሀ” አላት ፡ እየጎረ ።

በጣሳ አቀረበችለት ። ያን ጉርጉጭ አደረገና ጉሮሮውን
ጠራርጎ የጠቀለለውን ከመጉረሱ በፊት ለወሬ ሲያቆበቁብ
አንጓች ቀድማው “ምነው ሌሎች ሰዎች እንዲህ አይሉ?
አንተ ብቻ ነህ መአት የምታወራው ። ይኸ ፖለቲካህ …ዋ!”
አለችው ንዴት እየተናነቃት ።

“መአት ይፍላብሽ!” አለና የጠቀለለውን ጎረሰ ።
ተቻኩሎ ዋጠና “ሁሉም ያውቀዋል ። ያንቺ ማይምነት ነው
የበጠበጠኝ ። የአረብ ተንኮል ማን ጠፍቶት? ብቻ… እስራ
ኤል ነቅታበታለች ። የቀመመውን መርዝ መልሳ ትረጭበታ
ለች ። ያኔ አረብ የእጁን ያገኛል! እስራኤል ማርከሻውን
የፈለሰፈችው ከፈረንሳይ ጋር ነው ይባላል ። ይኸ የአይጥ
መግደያው ዱቄት እንዳይመስልሽ! አለምን በሃያ አራት
ሰዓት ፀጥ ጭጭ የሚያደርግ ፡ እንደጢስ የሚተን መርዝ
ነው” ብሏት ባልቻ በተረፈው የጣሳ ውሀ እጆቹን ተለቃል
ቆና ተጉሞጥሙጦ ራዲዮውን በማንጠልጠል ወደ ‘ቢሮው’
ገባ ።

የፀጉር ቤቷን መስኮትና በር ወለል አድርጎ ከፍቶ
ወንበር ላይ ተቀመጠና መልኩን በመስተወቱ እየተመለከተ



ፂሙን ደባበሰ ። …አንደኛውን የመቀምቀሚያ መኪኔታ
አንስቶ ከአፍንጫው ስር ችፍግ ብሎ የበቀለውን ፂሙን
መከርከም ያዘ ።

በግራ እጁ አራት ኮቶች ፡ በትከሻው ሁለት ሱሪዎች
ያንጠለጠለና በቀኝ ክንዱ ሶስት ሰአቶች አጥልቆ በጣቶቹ
ሜፍ ደማቅ አረንጓዴ ተካፋች ሹራብ የያዘ ሰው ወደ ፀጉር
ቤቷ ገባ ። የከተማይቱ እውቅ አዟሪ ነጋዴ ገበየሁ የተባለ
ወዳጁ ነው ። አምስት ሰአት ገደማ ሆኗል ።

“ባልቻ ፡ እንኳን አደረሰህ!” አለው በፈገግታ ።

“እንኳን አብሮ አደረሰን!”

“በአሉ እንዴት ነው?”

“ጥሩ ነው!”

“ምን ዜና አለ?” አለው ባልቻ በመስተዋቱ ውስጥ
እየተመለከተው ።

“ምን አለ ብለህ ነው?” ሲል ገበየሁ በማቅማማት
ጀመረና “ቅድም ትሁኔ ቤት ጐራ ብዬ ሳለሁ ‘የተባበሩት
መንግስታት ስብሰባ ጀምረዋል’ ሲል ራዲዮው ጆሮዬ ጥልቅ
አለ ። ምን ጉዳይ እንዳላቸው እንጃ!” አለ ትከሻውን
እየሰበቀ።

“እውነትህን ነው?” አለ ባልቻ ቀልጠፍ ብሎ ወደ
እርሱው በመዞር ። “ምን እባክህ ከዚች ገልቱ ጋር ስነታረክ
ወሬ አመለጠኝ” በማለት በግምባሩ አንጓች ወዳለችበት ጓዳ
ጠቆመው ።

“በኋላ ይደግመው የለ!”

“እሱማ ነው ። ግን ወሬ እሚጣፍጠው በትኩሱ ሲሆን
ነው ። ከጀርመንም ፡ ከቢቢሲም አላጣውም ። ለመሆኑ የኛው
ራዲዮ ነው እንዲያ ያለው?” ሲል ጠየቀው ፡ ገበየሁን ።

ወሬያቸውን ለማራዘም እንጂ ፡ በዚያን ሰአት በአማርኛ የሚያስተላልፍ የውጭ ሀገር ራዲዮ ጣቢያ እንደሌለ ልቦናው ያውቀዋል ።

"የጀርመን ጣቢያ ሳይሆን ይቀራል?" አለ ገበየሁ ተቻኩሎ ። ባልቻ የልቡ ስለደረሰለት ከአንጀቱ ከትከት ብሎ ሳቀበትና "አዬ ሞኝ ! አሁን በዚህ ሰአት የጀርመን ራዲዮ አለ? አይ ማይምነት!" በማለት ተሳለቀበት ።

"ለምን አይኖርም?" አለው ገበየሁ ። ይህን ያህል የሚያስተቸው ጉዳይ አልመሰለውም ።

"አይኖርማ!" ሲል መለሰለት ባልቻ ። "እዚህ ቀን ሲሆን እዚያ ይመሻል ። እዚያ ሲመሽ ደግሞ ፡ እዚህ ቀን ይሆናል ። እናም ባልከኝ ሰአት የጀርመን ሰው እንቅልፉን ስለሚለጥጥ እንደማይሆን አውቀዋለሁ ።"

"በቃ ተወው! ያለመማሬን ጉድ ያወቅሁት አሁን ገና ነው" ሲል ገበየሁ ትምህርቱን ተቀበለው ።

ባልቻም በአዋቂነቱ ተኩራርቶ ፈገግ አለና "ጀርመን ጣቢያን እወደዋለሁ ። አይዋሽም'ኮ! ሃቁን ነው ፍርጥ የሚያደርገው" በማለት ወደ ተጨማሪ ማብራሪያ ተሸጋገረ ።

ገበየሁ ቁጥርጥር ፀጉሩን ደባበሰና በውኃ የተሞላውን ጠርሙስ አንስቶ አናቱ ላይ አርከፍክፎ አሸው ። ከዚያም ወደ መስተዋቱ ተጠግቶ እያበጠረ "ስብሰባውን የከፈተው የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ነው' ሲል የሰማሁ መሰለኝ ። ስለምን ይሆን የሚወያዩት?" የሚል ጥያቄ አቀረበ።

"ዘንድሮ አማሪካ አቅለብልቦታል ። ጥሉ ከአለም ጋር በኢኮኖሚ ነው ። ሁልጊዜ ። ቆይ …ቆይ! ቻይና በስብሰባው ተገኝታለች አልተገኘችም?" ሲል የራሱን ጥያቄ ሰነዘረለት ።



"ይህን እንኳ እንጃ!" አለው ገበየሁ ። "የያዝኩት ልብስም ሆነ ሰአት ላይ አይኑን የሚጥል ስላጣሁ ከትሁኔ ቤት ወጣሁ ።"

"ቻይና ካልተገኘች ደግሞ ነገር አለማለት ነው ። አማሪካና ቻይና አይጥና ድመት ናቸው ። ቻይኖች የዋህ መስለው ልባቸው እማይገኝ ብልሆች ናቸው ። ደሞ ታያለህ ፣ ከአማሪካ ጋር ጦርነት ያነሳሉ" አለ ባልቻ ።

"ቻይኖች እኒህ የወልደያ–ደሴን መንገድ የሚሰሩት አይነ ጭፍኖቹ አይደሉም?"

"አዎ ፣ ዋዛ እንዳይመስሉህ! አይናቸው ቢጨፈን አእምሮዋቸው ክፍት ነው ። እንደ እስራኤል የጥበብ ሰዎች ናቸው ። በዚህ ላይ መንግስታቸው ሶሻሊዝም ስለሆነ ከመስኮብ ጋር ይገጥማሉ ። የህዝባቸው ቁጥርም የትየለሌ!"

"ጦርነቷ አይከፈቱ እንጂ ከከፈቱ አሜሪካስ ወዳጅ ያጣል ብለህ?" አለ ገበየሁ ፣ አበጣጥሮ ጨርሶ ሚዶውን ከሥፍራው እያኖረለት ።

"እስቲ በል ማ?" ባልቻ ክርክር ለመክፈት ቋመጠ ።

"ለምሳሌ ጥሊያን!" አለው ገበየሁ ።

"ወይድ! 'ሥጋ ቁጠር ቢሉት ጣፊያ' አሉ ። ጥሊያን ባስታውን ይጠቅልል እንጂ ፣ ደሞ እሱ ብሎ!" የሚል ተቃውሞውን ባልቻ ወረወረ ።

ገበየሁ "እንግሊዝስ? ፈረንሣይስ?…" እያለ በመቀጠል ክርክራቸውን ለማጧጧፍ በማሰላሰል ላይ እያለ ፡ በተንዠረገገ አዲስ ካኪ ሳሪያን ኮትና ባት ተግማሽ ሱሪ ያጌጠ ጐፈሪያም ዳንዴ ፣ መውዜር ጠመንጃውን እንዳነገተ ወደ ፀጉር ቤቱ ገብቶ ቆመ ። ሰላምታ አላቀረበም ። ሰው እንደሚፈልግ ሁሉ በድንገት ዘው ብሎ ገብቶ በመገተሩ

ሁሉቱም ደነገጡ ።

"ምን ነበር?" አለው ባልቻ ፣ ሽቅብ ቁልቁል እየተመለከተው ።

"ፀጉሬን ልቆረጥ!" ሲል መለሰለት ሰውዬው ጐፈሬውን እየነካካ ።

"አንድ ብር ትከፍላለህ" ብሎት ባልቻ ወደሚቀመጥበት ወንበር በጣቱ ጠቆመው ።

ሰውዬው አቅማማና ጠመንጃውን ጭኑ ላይ እንዳጋደመ ቁጭ አለ ፣ በተሰነጣጠቀው መስተዋት መልኩን እየተመለካከተ ።

ባልቻ የሰቀለውን አንሶላ አንስቶ በሰውዬው ትከሻ ላይ ጣል አደረገና ፀጉሩ ላይ ውሃ ካርከፈከፈበት በኋላ አበጠረለት። ቀጥሎም ማበጠሪያውን ወደግራ እጁ አዛውሮ በቀኝ እጁ መቀሱን እያንቀጫቀጨ የሰውዬውን ፀጉር አሸተተው ። ብሽ ስላለው ፊቱን ቅጭም አደረገና "ቅቤ አለው እንዴ ፀጉርህ?" የሚል ጥያቄ ለሰውዬው አቀረበለት ።

"ቢኖርበትሳ?" ሲል መለሰለት ሰውዬው ቆጣ ብሎ ።

"መቀስ ይጐዳብኛል!"

"አላቅልህም! ብሬን ከፍዬ ነው'ኮ እምቆረጠው ።"

"ወንድሜ ቅቤያማ ፀጉር መቀስ ይጐዳል ። የያዝኩት መቀስ ደሞ የአረብ መቀስ ነው ። ጥንካሬ የለውም ። የጀርመን ቢሆን እንኳ እንዳሻው! በጥንካሬው ወደር አይገኝለትም ። ለማንኛውም ገንዘብ ትጨምራለህ" ሲል አቋሙን ገለጸለት ።

"ስንት?"

"ሃያ አምስት ሳንቲም ።"

"እጨምራለሁ ። ቁረጠኝ ።"

ባልቻ የሰውዬውን ፀጉር ከበስተኋላው ማሳጠር



ጀመረ።

"ወደ አዲሳባ ስለምወጣ ያማረ ከመከም አድርግልኝ" በማለት ሰውዬው የሚፈልገውንም የቁርጥ ዐይነት ጠቆመው።

"እሱን ለኔው ተወው!" አለውና ባልቻ ፣ "ለምን ጉዳይ ነው ወደ አዲሳባ የምትሄድ?" የሚል ጥያቄ አቀረበለት።

"ከታናሽ ወንድሜ ጋር አገር ለማየት ።"

"ወንድምህ ከዚያ ነዋሪ ነው?"

"አይ!" አለው ሰውዬው ፣ "የክልል ተመራጭ ስለሆነ ለሸንጐ ስብሰባ ነው የሚሄደው ።"

"ለባርላማ ስብሰባ ማለትህ ነው?" ሲል ገበየሁ ጣልቃ ገባ ።

"አንተ ደሞ!" አለው ባልቻ "ባርላማ ይባል ሸንጐ ፣ ያው ስብሰባ ነው ። እርግጥ ባርላማና ሸንጐ ልዩነት አላቸው ። ባርላማ የፊውዳሊዝም ስብሰባ ሲሆን ፣ ሸንጐ ደሞ የሶሻሊዝም ነው" የሚል ትምህርት አከለለት ።

"ሽቶስ አለህ?" የሰውዬው ጥያቄ ነበር ።

"አለኝ ። ግን ገንዘብ ያስጨምራል" አለው ባልቻ ።

"ስንት?"

"ሃያ አምስት ።"

"ይሁን ! ብቻ ሸጋ አርገህ ቁረጠኝ ።"

"ልብ በል! ብር ተሃምሳ መሆኑ ነው!"

"ሂሳቡ መች ጠፋኝ አልኩህ! ጣቴን እምጠባ ህፃን መሰልኩህ ወይስ ባላገርነቴን አይተህ ማሾፍህ ነው?" ሲል

ሰውዬው ቱግ አለ ።

ባልቻ ተርበተበተ ። "በል ተወው ወንድሜ! ባመት ባል ምድር ከፉ አንዳረስ ።"

ለገበየሁም የሰውየው ሁኔታ አላማረውም ። ልውጣ ወይስ ልቆይ እያለ ሲያወላውል ተላይነህ የሚባል ከሲታና ጐባጣ ሰው በአንገቱ ዙሪያ ጠምጥሞ የሚቋጨውን ነጠላ እያፍተለተለ ዘው አለ ።

"እንኳን ላዲሱ ዓመት አደረሳችሁ" አለና ከመቸኮሉ የተነሳ ምላሻቸውን እንኳ ሳይጠብቅ "ባልቻ ፣ ዜና አዳመጥክ? አንድ የፈረንሳይ አሮብላን ተጠለፈኮ!" የሚል ወሬውን አስቀደመ ።

"እንዴት ባክህ?" ሲል ባልቻ ከአፉ ቀልቦ መቀሱን በአየር ላይ እያንቀጫቀጨ ቆመ ።

"እንዴት እንደሆነ ምኑን አውቄው" በማለት ተላይነህ መለሰለት ።

"ጠላፊውስ ማን ነው?" የገበየሁ ጥያቄ ነበር ።

"ወዴት አገር ነበር እሚሄደው?" ሲል ባልቻም የበኩሉን ጥያቄ አቀረበ ።

"ተጠለፈ መባሉን እንጂ ሌላ ሌላው አልተያዘልኝም" በማለት ተላይነህ አጠቃሎ መለሰላቸው ።

"ይኸውልሃ !" አለ ባልቻ ገበየሁን በዓይኑ ጠቅሶ ። "በተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ላይ ቻይና አልተገኘችም ማለት ነው ። ይኸ እንደሚሆን ታይቶኝ ነበር ። "

"ቻይናና ፈረንሳይ ጠበኞች ናቸው?" ሲል ተላይነህ ጠየቀው ።



"ቻይና እንደመስኮብ መንግስቷ ሶሻሊዝም ነው ። እነፈረንሳይ ፣ እነእግሊዝና እነአሜሪካ ደሞ መንግስታቸው ኢምፔሪያሊዝም ነው ። ታዲያ ..." እያለ ማብራራት እንደጀመረ ገበየሁ ጣልቃ ገባ ።

"ጀርመንስ?"

"ጀርመን እንኳ ቅይጥ ነው ። እንዲህ በፀሐይ መውጫ በኩል" በማለት እጆቹን ዘርግቶ "የሶሻሊዝም ፣ በወዲህ በፀሐይ መግቢያ በኩል ደሞ የኢምፔሪያሊዝም መንግሥት አለው ። ሁለቱ ግዛቶቹ በግምብ የተለዩ ቢሆኑም ፣ ህዝቡ በግምቡ ላይ እየተንጠላጠለ መፋጠጥ ከጀመረ ስንትና ስንት ዓመቱ!"

"ምናለ ይኸን ፖለቲካችሁን ብትተዉ!" አለ ሰውየው፡ "ምናለ ይኸን ፖለቲካችሁን ብትተዉ!" አለ ሰውየው፡

"ምናለ ይኸን ፖለቲካችሁን ብትተዉ!" አለ ሰውየው፡ በተቀመጠበት ቆርጠጥ ቆርጠጥ እያለ ። "ታወሩ እንደሁ ስለአገራችን ፣ ስለመንግሥታችን ፣ አውሩ ። እኛ ስለተቀረው ምን አግብቶን? ይህ ባህርማዶ እንጣጥ ብሎ ተሻግሮ በማያውቁት አገር መዳከር ምን ይባላል?"

ባልቻ ከድንጋጤው የተነሳ ከሰውዬው ማጅራት ወጣ ብሎ በመቀሱ ጭብጥ ሙሉ ፀጉር አነሳ ። ሳያስበው ያደረገው ጥፋት ነበር ። ፀጉሩን እንደጨበጠ አፉን ከፍቶ ሲንቀጠቀጥ ቆየና በሰውዬው ጀርባ ቁልቁል ለቆት ላቡን ጠራረገ ። መላጣውን ስፍራ ለመድፈን ከላይና ከታች ፣ ከግራና ከቀኝ ማበጣጠር ሞከረ ። ፈጽሞ የማይቻል ሆነበት ። እናም ከዚያ በመነሳት ፣ በሁለቱ ጆሮዎቹ አቅጣጫ ጥቂት ከፍ ብሎ በመቀሱ ቀጭን መሥመር አወጣና በቦጨቀው ልክ የሰውዬውን ፀጉር ዙሪያውን መደመደው ።

ይሄኔ ገበየሁ "ዞር ዞር ብዬ መጣሁ" ብሎ ውልቅ አለ ። ተላይነህም አፍታ ሳይቆይ መሰስ ብሎ ወጣ ። ባልቻና ሰውዬው ብቻ ቀሩ ።

ባልቻም ስራውን ወዲያው አቀላጥፎ ፣ የጥራቱን ውጤት ለመገምገም ያህል "እስቲ ወደቀኝህ ዞር በል" አለው ሰውዬውን ።

ሰውዬው ብድግ ሊልበት ሲል የበስተማጅራቱን ኮሌታ ጨምድዶ ያዘና መልሶ አስቀመጠው ።

"እስቲ ደግሞ አሁን ወደ ግራ ።"

ሰውዬው እንደተቀመጠ ፊቱን ወደ ጎዳ አዞረለት ።

"ጥሩ ነው!" ብሎት ባልቻ አንሶላውን ከትከሻው ላይ አወረደለት ። ከአሮጌዎቹ ፎጣዎችም አንዱን አንስቶ ፊቱን አበስ አበስ ሲያደርግለት የፀጉር ብናኝ ባፍንጫው ገብቶበት ኖሮ ሰውዬው ደጋግሞ አስነጠሰው ።

"ይማርህ!… ይማርህ!… ይማርህ!" እያለው ባልቻም ጐንበስ ቀና አለለት ።

ትንፋሹ ሲመለስለት ሰውዬው ወደ መስተዋቱ ጠጋ አለ ። የገዛ መልኩ አጠራጥሮት አይኖቹን ከፊት ከደን አደረገ።

"ቆይማ! ከወደ ግምባርህ ትንሽ ይቀረዋል መሰል" በማለት ባልቻ መልሶ አስቀምጦት አፍንጫውን ካጠላው ጐፈሬው በመጠኑ ከርክሞለት ፀጉሩን ከግምባሩና ከአናቱ በሚገባ ተመተመለት ።

"እኽ!" አለ ሰውዬው መልኩን በመስተዋቱ እያየ ፤ "ከመከም አለነበረ ያልኩህ?"



"አዬ የእኛ ሰው!" የሚል ምላሽ አመጣ ባልቻ ቀልጠፍ ብሎ ፤ "ያለ ከመከም ሌላ ቁርጥ አያውቅ ። ወደ አዲሳባ አይደል የምትሄድ?"

"ቢሆንስ ?"

"ያዲሳባን ተወውና ፣ ገና ደሴ ስትገባ የምታየው የፀጉር ቁርጥ አይነት ያይን አዋጅ ይሆንብሃል ። ጆንትራ እሚሉት አለ ፤ ከወደማጅራት እንደ አህያ ጅራት ቁልቁል ሾሎ እሚወርድ ፣ ወይ እንደፍየል ጭራ ሽቅብ እሚቀስር ፣ ካሊፎርኒያ እሚሉት አይነትም አለ ። ያ እንኳ ላንተ አይሆንም ። የአሜሪካ ነው" የሚል ሰፊ ማብራሪያ ሰጠው ።

"ይኸስ ምን እሚሉት ነው?" ሲል ጠየቀው ሰውዬው በጉጉት ።

"ሙኒክ ይባላል ። የጀርመን ነው" አለው ባልቻ አፉ እንዳመጣለት ።

ገና ያልሰማውና ያላየው ሆኖበት እንጂ ፣ በአጋጣሚ የደረሰበት ቁርጥ እንኳ 'ፓንክ' የሚባለው ዝርያ ነበር ።

ሰውዬው ሳቅ ብሎ ከወንበሩ ተነሳ ። ጠመንጃውን ጉልበቶቹ መሀል አቁሞ ፣ ኩራት ኩራት እያለው ከሳሪያን ኮቱ ደረት ኪስ ሁለት አሮጌ ብሮች መዝዞ ፣ እላፊ ሂሳብ እንዳያመልጠው እያንዳንዳቸውን አራገፈና አስጨብጦት "መልሱን ፣ ቶሎ በል" አለው ።

"ቆየኝማ ። እዚችው አረፍ በል ። ከሃጂ ኡስማን ሱቅ መንዝሬልህ ልምጣ" ብሎት ባልቻ እየሮጠ ወጣ ።

ሰውዬው ወደ መስተዋቱ ተጠግቶ እየተዟዟረ መልኩን ደጋግሞ አየ ። አልመጣልህ ብሎት ግራ በተጋባ መንፈስ

ራቅ አለና እንደገና ተመለከተው ። ጥቁር ቆብ የደፋ መሰለውና አማተበ ።

እንዲህ በመቅበጥበጥ ላይ ሳለ ባልቻ ተመልሶ መልሱን ሰጠው ።

"በዚህ ቁመናህና በዚህ ቁርጥህ ሎቲ ብታንጠለጥል!··" በሚሉ ቃላት እየሸነገለው እበር አደረሰው ።

"እዬዬዬ!" አለው ሰውዬው ፣ "ደን ጥበቃ እየተባለ ዝሆንና አውራሪስ መጣል ከቀረ በስንት ዘበኑ!"

"በል ፣ በደህና ያግባህ!" አለው ባልቻ ፣ በፈለሰፈው የፀጉር ቁርጥ እየተገረመ ።

"አሜን!"

ባልቻ አንገቱን ወደ ጓዳ ገባ አድርጐ "በይ ፣ በዚህ እንደሚሆን አድርጊ" ሲል ለአንጓች ብሩን ወርውሮላት ፣ በሃምሳዋ ሳንቲም አንድ ሁለት ሊል ወደ ትሁኔ ቤት ተፈተለከ ።

# ባለ ጉዳይ

ተባይ የወረሣትና የተቦጫጨቀች ቡናማ ሸሚዛቸውን ገልብ ጠው ለፀሐይ ዘርግተዋታል ። አጠገቧ ቁጢጥ ብለው ፣ የፀሐዩ ግለት ሲያይልባቸው እየተንፈራፈሩ ብቅ የሚሉትን ተባዮች እየለቀሙ በአውራጣታቸው ቀጭ ያደርጓቸዋል ፣ አባ እንቀር ሻው ።

ቀዬው ጭር ያለ ነው ፣ የሠፈሩ ቆሻሻ የሚከመርበት ። አልፎ አልፎ ብቻ አንዳንድ ሰዎች ውልብ ሲሉ ይታያሉ ።



ሊፀዳዱ ። የሠፈሩ ህፃናት መጫወቻ ለማግኘት የቆሻሻውን ቁልል ያተራምሳሉ ። ቁልሉ ቆሻሻ—የፀሐይዋን ግለት ሲቀበል አካባቢውን የሚያጥነው ግማት ለጉድ ነው ።

ረሃብና እርጅና ጓዛቸውን ጠቅልለው የሠፈሩባቸው አንድ አይናው አዛውንት አባ እንቀርሻው ፣ ለፀሃይ የዘረጓትን የተበሳሳች ሸሚዛቸውን አንስተው አራግፈው ለበሷት ። የነተበ ዐመድማ ጋቢያቸውን ከደረቡ በኋላ ሰኢስ ጠጥታ የቀላች ዘንጋቸውን ወደላይ ቀስረው ፣ ትልቁን ዋርካ ሽቅብ አያዩ የራስ—በራስ ሙግታቸውን ተያያዙት ፣ በንዴት እየተርገፈገፉ ።

"አዳፋ ብለብስ ፣ አፈ—ዶማ ብሆን ማንን ጐዳሁ ? ግራ ቀኝ አሟግተው ተረትተሃል ቢሉኝ ምናለ ? ሰባት ዓመታት ሙሉ ከራቦር—ጠሐፊ ራቦር ጠሐፊ ስዞር ጅስሜ አልቆ ፣ የሰው ውራጅ ሆኜ ብቀር ምን ሊጠቀሙ !?" ንግግራቸውን ገታ አደረጉና ዘንጋቸውን ወደ ትልቁ ዋርካ እንደቀሰሩ አፍጠው ተመለከቱት ።

ዋርካው አባ እንቀርሻው ለተናገሩት መልስ የሚሰጣቸው አልሆነም ። በሞገሱ ተኩራርቶ ቁልቁል በንቀት የሚመለከታቸው መስሏቸው እሮሮአቸው ገነፈለ ። "ጥንት ጉንዶ ማር ፣ እሥራት ፣ የቆሎ ፣ የሣርና የውሃ ፣ የስልከኛ ፣ የምልምል ፣ የመስቀል ፣ የቋሳ ··· ምን ሥፍር ቁጥር አለው ? ··· በሚሉት የግብር አይነት ወሎ—ወሎዬ ምን ያላየው አበሳ አለ ? ዛሬም አሳሩ ብዙ ነው ። ሙግት ቢመጣ በሱ ··· እህል ቢያር የሱ ··· ለጦርነት ቢመለመል እሱ ··· የነፍጥ መራኮቻና መረሟመጃ ቀየ የሱ ··· ዳኛ ከነሱ ··· አየ ጉድ !

ጥራሪ ፍሪደኝ ! የወለሀ—ማርያም አውድማ ይታዘባቸው ! ጡረኞች !” አሉና አፈር የጠጣ ጋቢያቸውን አራግፈው ዘንጋቸውን እየተደገፉ ራፖር ፀሐፊ ፍለጋ ፤ ጀርባቸውን ለዋርካው ሰጥተው ወደ መሀል ከተማው ማዝገም ጀመሩ ። …

ለሰባት ዓመት ያክል ፍትሀ ያጡበት ጉዳይ አላቸው ። ፍትሀ ፍለጋ ያልዞሩበት ቦታ የለም ። በየአጋጣሚው የገኙትን ፖሊስ ሁሉ እያስቆሙ ጉዳያቸውን በዝርዝር ለማሳወቅ ቢሞክሩም ንግግራቸውን አስኪጨርሱ እንኳ ያደመጣቸው አንድም የለም ። ፋይላቸውን ታቅፈው ገና ጠጋ ሲሉት ለልመና የመጡ እየመሰለው ‘እግዜር ይስጥዎ !’ እያለ የሚርቃቸው ብዙ ነው ።

ለዚህ ጉዳያቸው የነበራቸውን ገንዘብ ሁሉ ጨርሰዋል ። በተለያዩ የራፖር ፀሐፊዎች የተለያየ ማመልከቻ አፅፈዋል ። ለክላሰር ፤ ለቴምብር ፤ ለፍርድ ቤት አንጋቾች ጉቦ … ያወጡት ወጪ ቀላል አልነበረም ።

የዚህ ሁሉ ውጣ—ውረድ የከፋ ድህነት ውስጥ ከቶአቸዋል ። ንዴትና እልሀ አስከትሎባቸዋል ። ብቻቸውንም ያወራሉ አድማጭ ባይኖራቸውም ለራሳቸው ሲያወሩ የፍትሀ ጭላንጭል ያገኙ ያክል ቀለል ይላቸዋል ። ተስፋ እየታያቸው ይፅናኑባታል ።

ሁነኛ የራፖር ፀሐፊ ማግኘት ቀላል አልሆነላቸውም ። አብዛኞቹን የወልዲያ ከተማን ራፖር ፀሐፊዎች አዳርሰዋል ። የሁሉም አልጣማቸውም ። እስከአሁን ያልሞከሩትን ማፈላለግ ጀምረዋል ፤ እያጠያየቁ በቅርቡ ከውጭ ወደ ወልዲያ



የመጣ እውቅ ሰው መኖሩን ሰምተው ወደሱ ለመሄድ ልባቸው ቆመ ።

* * *

ሰውየው በእርግጥም ወልዲያ ከገባ ገና መንፈቅ ቢሆነው ነው ።

የተለያዩ ዶሴዎችን ፤ የተጨረማመቱ ካርቦኖችንና ሉክ ወረቀቶችን ከተሸከመው አሮጌ ጠረጴዛ ጀርባ የቆሸሸ አንሶላ አገልድሞ ፤ እንደ ትላንት የገዛው ነብስ ይማር ሱፍ ሱሪው ረዝሞበት ኖሮ አጥፎ እየቀመቀመ አጠገቡ ካለ አንድ ባለ ጉዳይ ጋር ያወጋል ። ባለአንዲት ክፍሏ ደሳሳ ጐጆው መኖሪያውም ፤ ቢሮውም ናት ።

“የሰማንያ ፊርማ ሳይኖረን ፤ በወደድኩሽ—ወደድኩሀ በአንድ ጣራ ስር መንፈቅ ለማይሞላ ግዜ አብረን በኖርን ፤ ስንቋን ደባልቀን አንድ ማዕድ ላይ በቀረብን ብቻ … ወደኋላው ባንስማማና ልባችን እየቅል ሆኖ ብንላቀቅ ‘ንብረት እኩል ይገባኛል’ ብላ ብትከሰኝ ሕጉ ይደግፋታል ?” ሲል ራፖር ፀሐፊውን ጠየቀ ።

“ይኸንን ሀሳብሀን ለፍርድ ቤቱ አልፃፍክም ኖሯል ?” አለው ራፖር ፀሐፊው ቀና ብሎ ሌላ ዶቃ ክር በመርፌው ቀዳዳ እየከተተ ።

“ምን ዋጋ አለው ?” አለና ሰውየው ከንፈሩን ነከሰ ። “በማይረባ ፀሐፊ አፅፌ ለዳኛው ብሰጣቸው ‘ጭብጥ የለውም !’ አሉኝ ። ሁለት ብር እኮ ነው የከፈልኩት ። ጉድ ሠራኝ !” በቁጭት ተወራጨ ።

"የህግ ነገር ዋዛ አይደለማ !" ፀሐፊው በኩራት ተኮፈሰ ፣ 'ከእኔ ወዲያ ፀሐፊ !' በሚል ስሜት ። ቀጠለና "የህግ ፅሁፍ ማንም የሚፅፈው ነገር አይደለም ። ለመፃፍማ ዛሬ ማን የማይፅፍ አለ ? ቁም ነገሩ ግን ባለጋራውን ሊረታ የፈለገ ነገረኛ ዳኛውን የሚያዋዛ ፣ ዳኛውን እያከበረ የሚያግባባ ፣ በተለይ ቁልጭ ያለች የህግ አንቀጽ ጠቅሶ ሲያቀርብ ነው እንጂ አለዚያማ … በዋል ፈሰስ ነው" አለው የቋጠረውን ክር በጥርሱ እየቆረጠ ።

ራፖር ፀሐፊው ከሌሎቹ ፀሐፊዎች የሚሻልበት ሁኔታ ስላለው ገና ከመምጣቱ በህብረተሰቡ ዘንድ ታዋቂነትን አትርፏል ። ፍርድ ቤቶች አካባቢ እየተዘዋወረ በየአጋጣሚው የሚያደምጠውን የህግ ቁጥር ሁሉ ለአንድ ወቅት ያገለግላል በሚል መንፈስ ሲመዘግብና ሲያጠና የኖረ ነው ። ደሴና አዲስ አበባ በሚመላለሱ ነጋዴዎች የነጋሪት ጋዜጣ ያስመጣል ። ጊዜ ያለፈባቸው ቢሆኑም የተለያዩ ጋዜጦችን ይሰበስባል ፣ በተለይ ለህግ አምድ ልዩ ሱስ አለው ።

በአነጋገሩ ጥራዝ—ነጠቅ በመሆኑ የፈረንጅኛ ቃላትን በመደባለቅ የመጠቀ የህግ አዋቂ መስሎ ይቀርባል ። የሌሎችን ራፖር ፀሐፊዎች ስም ያጠፋል ፣ ችሎታ እንደሌላቸው በግልጽ በመናገር ። በባለጉዳዮችና በዳኞች መካከል ጉቦ ስለሚያቀባብል እና በመካከሉም ስለሚጎርስ እሱም በሌሎቹ ፀሐፊዎች ይጠላል ። ቢሆንም የደምበኛው ብዛት በሽ—በሽ ነው ። በአጠቃላይ በከተማው ከሱ ወዲያ ራፖር ፀሐፊ ያለ አይመስልም ።



"ታዲያ እንዴት ላድርግ ? የማንም ጋለሞታ መጥሪያ እያስወጣች ፍርድ ቤት ስታንከራትተኝ ትልቅ ውርደት አይደለም ?" አለ ሰውዬው ቀኝ እጁን ጨብጦ ጭኑን መታ መታ እያደረገ ።

"ላንተ ጉዳይ መጠቀስ ያለበት የህግ አንቀጽ …" አለና ራፖር ፀሐፊው ጠረጴዛው ላይ ያለውን 'የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ' የሚለውን ጥራዝ ሲያገላብጥ "እንደምንዋላችሁ ቤቶች !?" አሉ አንድ አዛውንት አንገታቸውን ብቅ አድርገው ።

"እግዜር ይመስገን ! ይግቡ" አለና ፀሐፊው ተጣድፎ መለሰ ፣ ካርቶኖች የተነጠፉባትን መደብ እየመለከታቸው ።

ራፖር—ፀሐፊው ቀደም ሲል ችግሩን ሲያዋየው ለቆየው ባለ—ጉዳይ ቀጠሮ ሰጥቶ ፣ የቀመቀመውን ሱሪ አጠገቡ ወደሚገኝ የጠፍር አልጋው ላይ ወረወረና ያገለደመውን አንሶላ አጠበቀ ። መርፌዋንም ግድግዳ ላይ ሰካት ።

"ምን ነበር አባት ?" አለ እየተንጠራራ ። ሲንጠራራ የተቀመጠባት ወንበር ተንሳጠጠች ።

"ነገሬ ብርቱ ነው !" አሉና በረዥሙ ተነፈሱ አባ እንቀርሻው ፣ ያመለከታቸው መደብ ላይ እየተቀመጡ ።

በራ በሆነው ጭንቅላታቸው ላይ አንድ ወፈር ያለ አረንጓዴ ክር አዙረዋል ። ከዚሁ ጋር በተያያዘች አዳፋ እራፊ ጨርቅ ግራ ኣይናቸውን ሸፍነዋል ። የተጎሳቆለውና እንደ መነኩሴ ቆብ የተጣጠፈው ፊታቸው በእርጅና ላይ መከራ

የተደራረበባቸው መሆኑን ይመሰክራል ። ባጠለቁት ሰፊ ቁምጣ ግራ ጭናቸው በኩል ብልታቸው ብቅ ብሎ ይታያል ። እንደ ዋልካ መሬት የተሰነጣጠቁት የእግሮቻቸው ተረከዞች የሌት ቁርና የቀን ሃሩር እንደተፈራረቀባቸው ያስታውቃሉ ።

"አ/ዴተ ነው ነገሩ ! ክስ ነው ወይስ መልስ ?"

"አትቸኩል ልጄ ! 'እህ !' ብለህ አድምጠኝ ። ሁነኛ ጠሃፊ ነገርን ያደምጣል ። ነገሬ ብርቱ ነው ያልኩህ ያለምህኛት አይደለም ። ሰባት ዓመት ሙሉ ያንከራተተኝ ፣ አለጧሪ አለቀባሪ ያስቀረኝ ፣ የከተሜ ምጥዋተኛ ፣ የደጀ— ሰላም ቤተኛ ያደረገኝ ነገር ነው ። በይህ ነገር ከጠሐፊ— ጠሐፊ ስዞር የፈጀሁት ገንዘብ አይወጋም" አሉና በዘንጋቸው ጀርባቸውን አከክ—አከክ አደረጉ ።

"ቢሆንልኝ ብዬ ሙግት ከገባሁ ዘመን የለኝም ። ምን ዋጋ አለው ! በዚህ ላይ የዛሬ ዓመት ገደማ የከተማ ቀጣፊ አራት ባውንድ ቀማኝ !"

"የት አባቱንስ ! የሐማኛውን ስም ያውቁታል ?" አለና ራፖር ፀሐፊው አቋረጣትው ።

"ኤዲያ ! ምናለ ብታደምጠኝ !" በብስጭት እጆቻቸውን አወናጩፉ ። ተስፋ መቁረጣቸው ከፊታቸው ይነበባል ።

"ልብ ብለህ አድምጠኝ ! ከአፌ አትቀማኝ !" አሉና በቁጭት ዘንጋቸውን አጥብቀው ጨብጠው ወለሉን ወጋ ወጋ አደረጉት ። "በተወለደች በዓመቷ በምች እመም እናቷ ስትሞት እንደ እናት ፣ እንደ አባት ሆኜ አንዲት ልጄን ያሳደኳት እኔው ራሴ ነበርኩ ። በጀርባዬ አዝዬ ፣ የፍየል



ወተት እያጠባሁ ከስንት መዓት ያተረፍኳት መከራየን ቢልቻ ነው ፣ ምስለኔ የተወልኝ የዐውድማ ጥራጊ ለዕለት ጉርሳችን ባይበቃ ፣ ጥራሪ ወርጂ እንጨት ተሸክሜ ጉልት እያወጣሁ በማገኛት ቁጣሪ ለወግ ለማዕረግ አበቃኋት በምልበት ወቅት … ወይኔ እንቀርሻው ! የዘራነውን ሁሉ ተባይ ቢያጠፋብን ፣ ቀን እስኪያልፍ ያችኑ አንዲት ፍሬየን አስከትዬ እዚሁ ወልዲያ ገባሁ ። እንደ ባልንጀሮቿ ተላውሳ ጥቂት ቁጣሪ ብታገኝ ብየ ግራዝማች አበጋዝ ቤት አስቀጠርኳት ባግር ድና ።

"በተቀጠረች በአራት ወሯ የጌታየ የግራዝማች ልጅ ካሣሁን ድንግልናዋን ቢገሳት ፣ የፀነሰችውን እንኳ በሰላም እንዳትገላገልበት ፣ ቤተክስያን እንደገባች ውሻ ብጣሺን ብቻ አስይዘው አባረሯትና መግቢያ ቢጠፋት ተመልሳ እጄ ላይ ወደቀች ። ለማን አቤት ይሉታል ?"

"ለዕለት ስንቃችን ከተማ እየዞርን ውለን ፣ ማደሪያችን ደጀ ሰላም ሆኖ እያለ አንድ ሌሊት ውጋት ጡት ስሯን ቀስፎ ያዛትና እጄ ላይ አረፈች ። ዘመድ ወገን ስለሌለኝ እንበለ ፍታት ፣ እንበለ ፀሎት ቀን ተሌት ራሴ ጭራ ታች መሬት አዋልኳት ። ይኸን በደሌን ደጋግሜ ባመለክት ማን ይስማኝ ? የከሰስኩት ግራዝማች አበጋዝን … ዲታ! የጉባ ላፍቶ ተወላጅ ባላባት ! ልጄን ለሞት የዳረገ የጌታዬ የግራዝማች የበኩር ልጅ ! ህጉ ለሳቸው … የንጣቱ የማጣቱ ነገር የኔ ! ቆይማ …" አሉና ከውስጥ ኪሳቸው አንድ የተጣጠፈ ዶሴ አውጥተው ሳጡት ።

ራፖር ፀሐፊው ዶሴአቸውን ተቀብሎ ሲያገላብጥ አባ እንቀርሻው አንገትቻቸውን ደፍተው ጥቂት ከተከዙ በኋላ "አስተውለህ እየው ! ሃያ አንድ ወረቀት ነው ። ሰሚ ባገኝ ብየ ደጋግሜ ያጣፍኩት" አሉ ባሞጨሞጨችው ቀኝ አይናቸው ትክ ብለው እየተመለከቱት ።

ራፖር ፀሐፊው በባለ—ጉዳዮች ዘንድ ልዩ ግምት ከሚያስጡት ነገሮች ዋነኛው የሆነውንና በተለያዩ ክሮች የተተበተበውን ሰባራ መነፅሩን ዓይኖቹ ላይ ሰክቶ ዶሴአቸውን እያገላበጠ ማንበቡን ቀጠለ ። ጭንቅላቱን ግራ ቀኝ እያወዛወዘ ያልጐመጐማል ። አልፎ አልፎ ከንፈሩን ይመጣል ።

"ጥሩ አድርገህ ጣፍልኝ ! እጅህ ርጥብ ቢሆን ዕድሌን ልሞክር !" አሉት በረዥሙ እየተነፈሱ ።

ራፖር ፀሐፊው መልስ ሳይሰጣቸው ከአንድ ፋይል ወረቀት አወጣና ካርቦን ከተተበት ። ወደ አፍንጫው ጫፍ የወረደውን ሰባራ መነፅሩን ከፍ አድርጎ ዕለቱን መፃፍ ጀመረ ።

"አ ! አ !" አሉና አባ እንቀርሸው ራቦር ፀሐፊው ቀና ብሎ እንዲያያቸው አደረጉት ። "የጅህ ዋጋ ስንት እንደሆነ እንነጋገር ። በአራት ኮቢ አድርገህ ጣፍልኝ ። እንበለ ቀሪና እንበለ ቅጂ ሙግት ምን ዋጋ አለው ? አንድ ለአውራጃው ግዛት ፍርድ ቤት … አንድ ለቦሊስ … አንድ ደግሞ ለአውራጃው ገዢ … አንዱ የኔ ቀሪ ይሆናል ።" በግራቸው በኩል የነበረችውን ዘንጋቸውን ወደ ቀኛቸው አዞሩ ።

"ጥሩ ! እንግዲህ … እኔ የምፅፈው አንቀጽ ጠቅሽ ነው ። ለአራት ኮፒ አሉኝ ? እስክሪፒቶ ፣ ወረቀትና ካርቦን ተወደዷል ። በተለይ የእስክሪፒቶ ነገር ! የዛሬ እስኪሪፒቶ ገና አንድ ሳይሉበት ያልቃል ። አሁን ይቺ …" አለና ቀለሟ ታች የደረሰውን እስክሪፒቶ ከፍ አድርጎ አሳያቸው ። "ትላንት ገዝቻት ገና አራት ወረቀት ሳልፅፍባት ነው እንዲህ ያለቀችው ! ጉዳይዎ ደግሞ የዋዛ አይደለም ። ብዙ አንቀጽ መጥቀስ አለብኝ ። ስለዚህ አራት ብር ይከፍላሉ !" አለና ደፍጠጥ ባለው አፍንጫው ላይ የተፈናጠጠውን ሰባራ መነፅሩን ወደ ላይ ገፋ አድርጐ በእስክሪፒቶው ጠረጴዛውን መቆርቆር ጀመረ ።

"ይበዛብሃል ማለቴም አይደል ! ባይሆን ጥቂት ቀንስልኝ … ራብ አንጀቴን አጥፎታል ። የለምለም እንጀራ ሽታ በአይኔ እየዞረ ነው ። በደጅ—ሰላም ፍርፋሪ ትንፋሼ አለች ። እንደሚሆን አድርግልኝ ። ከልጆችህ ታገኘዋለህ ። የተማረ ሰው አይጨክንም ። …" ልመናቸውን አዥጐደጐዱት ።

"ይበሉ ሦስት ብር ይክፈሉ ! ምን ይደረግ ?" ወረቀቱንና ካርቦኑን ካስተካከለ በኋላ እስክሪፒቶውን ወጋ ።

አባ እንቀርሻው ከፍየል ቆለጥ ቆዳ የሠሯትን የገንዘብ ማስቀመጫ ከረጢታቸውን ከጉያቸው አካባቢ አወጡና የተጠፈረችበትን ጅማት ፈትተው ከውስጧ የተጣጠፉ ብሮችንና ሣንቲሞችን አወጡ ። አንዷ ብር ሌላ እንዳልደረበች ደጋግመው በማሸት እያረጋገጡ ፣ ሣንቲሞቹንም ጥርሳቸው ላይ እየከረከሩ ከለዩ በኋላ ሶስት ብር ሰጡት ። ሁለት ብሮችና የአንድ ብር ሣንቲሞች ።

ራፖር ፀሐፊው የተቀባላቸውን ሦስት ብር ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ አቀርቅሮ መፃፍ ጀምሯል ። የሚፅፋቸውን ቃላት ዝቅ ባለ ድምጽ ይናገራቸዋል ። የተጠጋገኑ የህግ መፃህፍትና የወየቡ ነጋሪት ጋዜጣዎችን ያገላብጣል ። ያልጐመጉማል ። የመደነቅ ፣ የመጨነቅ ፣ የመመራመር ስሜት ፊቱ ላይ እየተነበበበት ይፅፋል ።

"ለመንግሥቱ ታማኝ … ለህግ ተገዥ … የታዘዝኩትን የማላጐድል' በልበት !" አሉት አባ እንቀርቻው አንገታቸውን አስገው ።

ራፖር ፀሐፊው ያደመጣቸው አይመስልም ። ዝም ብሎ ይፅፋል ። ያልጐመጉማል ። ጣራው ላይ አፍጦ ያስባል ። ያሰላስላል ። ያረጀ የቀሚስ ትልታይ ከሸሚዙ ኪስ እያወጣ የአፍንጫውን ጫፍ ይጠርጋል ። አሥር ግዜ ሰባራ መነፅሩን ከፍ ያደርጋል ።

"'ለባንዲራዬ ሟች … ጧሪ የሌለኝ … የሰባ አራት ዓመት ሽማግሌ … አቅመ ደካማ' በልልኝ ! ዋናው ይኸ ነው !"

"ዝም ይበሉ አባት !" አላቸው ካቀረቀረበት ቀናብሎ ። "አይገባም ! ለኔ ይተዉት … ስጨርስ አነብልዎታለሁ ። እያደናቅፉኝ !" አለና አቀረቀረ ።

ዝምታ ሰፈነ ።

ወዲያውኑ አንዲት ወፍራም ሴትዮ እያለቀሱና እየተናፈጡ ገቡና "ጋሼ መርጊያው ! ቦሊሱ ማመልከቻ አስጥፌ እንድመጣ መክሮኛል ። ወይኔ ! እሱ ጉልበተኛ ሆኖ እኔን ሊጫወትብኝ !? … ሴተኛ አዳሪ የሆንኩት ወድጄ መሠለው እንዴ? … እኔን አታሎ ቤት ካዘጋኝ በኋላ ሂሳቤን ክፈለኝ ብለው አፍንጫዬን መታኝ ። አንድ ጫማውን ላስቀርበት ብሞክር አልቻልኩም !" ሴትዮዋ ያለቅሳሉ ። አንድ ወረቀት ይዘዋል ።

"ኧረ ይቆዩማ ! ሊበላሽብኝ ነው'ኮ ! ረጋ ይበሉ … የኔ ይለቅ !" አሉ አባ እንቀርቻው ሁለት እጆቻቸውን ወደ ሴትዬዋ ዘርግተው ፣ የሴትዬዋ ስሞታ የራፖር ፀሐፊውን ሃሳብ እንዳያደናቀፍባቸው እየሰጉ ።

ሴትየዋ እምባቸውን እየጠራረጉ ጥግ ተቀመጡ ። … አባ እንቀርቻው ፈራ ተባ እያሉ "'ከእግርዎ ሥር ወድቄ እኔ ባርያዎ የምለምነዎና በእግዜር ስም የምማጠንዎ … የሚል ጨምርበት ! አትርሳኝማ ልጂ !" አሉት ።

"ምን ያሉ በው ናትው !! ዝም ቢሉ ምናለበት ?" ራፖር ፀሐፊው ቱግ አለ ።

አባ እንቀርቻው አቀረቀሩና በትካዜ አንዲት ስንጥር አንስተው ወንከርከር ያለው ጥርሳቸውን እየወጉ በሀሳብ ሲብሰለሰሉ "ሳነብልዎት ፤ ያድምጡኝ !" አላቸው ሰባራ መነፅሩን ወደ ላይ ገፋ እያደረገ ።

አባ እንቀርቻው ከተቀመጡበት ብድግ ብለው አጠገቡ ቁጢጥ አሉና በተንቀሳቀሰ ቁጥር በምትንሳጠጠው ወንበር ላይ ወደተቀመጠው ፀሐፊ አንጋጠጡ ።

ፀሐፊው አፉንና አፍንጫውን አሁንም አሁንም ከኪሱ በሚጐትታት ብጣሽ ጨርቅ እየጠራረገ ፣ ጉሮሮውን ስሎ ማንበብ ጀመረ ። ቀኑንና ዓመተ ምህረቱን በዝቀተኛ ድምፅ ካነበነበ በኋላ ፣

“ለክቡር የየጁ አውራጃ ግዛት ፍርድ ቤት ።
ወልዲያ ።

ከሳሽ እኔ ··· ከማለቱ “ተበላሽቷል ልጄ ! እንዲህም አይደል የሚጣፈው !” አሉት አባ እንቀርሻው ተመልሰው መደቢ ላይ እየተቀመጡ ። ራፖር ፀሐፊውን በተስፋ መቁረጥና በብስጭት ተመለከቱት ። የሚናገሩት ነገር የጠፋባቸው ይመስላል ፤ በሁለት እጆቻቸው ጭንቅላታቸውን ደግፈው ያዩታል ።

“ምናለ ቢያስጨርሱኝ ?” የተማረረው ራፖር ፀሐፊ የጉሪጥ ተመለከታቸው ። አመለካከቱ የትዕግስቱን ማለቅ የሚያመለክት ነበር ።

“ምኑን ጨረስከው? ‘ለክቡር የየጁ አውራጃ ግዛት ፍርድ ቤት መሃል ዳኛ የተከበሩ ፊታውራሪ ገበየሁ’ ማለት ሲገባህ ጐረድከው! ቀጠልክና ደግሞ ‘ከሣሽ!’ —እንዴት ይቀበሉኛል? ‘እኔ ባሪያዎ’ ማለት ነበረብህ ። ማን አይዞህ ቢለኝ! ማን ቢከተለኝ? እግዜር ቢጣላኝ ነው አንተው!...”

ራፖር ፀሐፊው ፊቱን አኮሳትሮ ጠረጴዛውን በቡጢ ‘ዱ! ዱ!’ አደረገውና “ሌላ ፀሐፊ ይፈልጉ! ምን ያሉ ሰው ናቸው?” አለ ።

“አንተ ምናለብህ ? ድፍረት የተመላበት ጥሁፍ ይዤ ብቀርብ የምቀጣው እኔ! ካልሆነልህ ምን ይደረግ? እንደለመደብኝ ልንከራተተው እንጂ!” አሉና ብድግ አሉ ።

“ከኔ የተሻለ ካገኙ ይሞክሩ !” አለና ራፖር ፀሐፊው ፈገግ አለ ፤ ሊያባጫቸው ። ቀጠለና “የከሰርኩትን ወረቀትና ካርቦን ሂሣብ እቆርጣለሁ ። በዛሬ የገበያ ውድነት ቀልድ



የለም ! አንድ ብር ቆርጫለሁ!” አለ ሁለቱን ባሮች የያዘውን ቀኝ እጁን እየዘረጋላቸው ።

“በምን ምህኛት? ያበላሸኸው ራስህ! መልሰህ እኔኑ ለምን ትቆርጥብኛለህ? በህግ አምላክ!...በባንዲራው! ...በመንግሥት! ...በኋላ በምን ተከሰስኩ እንዳትል...”

ራፖር ፀሐፊው ከተቀመጠበት ወንበር ብድግ አለና “አሁን ከቤቴ ይውጡ! ካለበለዚያ ግን ሆን ብለው ስራየን በማንቋሸሽና እንዲሁም አለአግባብ የግራዝማች አበጋዝን ስም ለማጥፋት በማን አለብኝነት ተነሳስተው ለፈፀሙት ወንጀል አንቀጽ ጠቅሼ ፡ እዝባር አድርጌ የአስቸኳይ ክስ ማመልከቻየን ለአውራጃው ዐቃቢ ህግ አቀርባለሁ!

“እንዲያውም ከማን እንደተላኩ ሳይታወቅ ‘ተንገላታሁ...ተረገጥኩ...’ እያሉ ለድሃ የቆመውን መንግሥት ፍትህ እንደማይሰጥ አድርገው የሚያማርሩ በመሆንዎ በጥብቅ እንዲመረመሩ ለአውራጃው ፖሊስ ህግ አስከባሪና የፀጥታ ሹም በአስቸኳይ አስታውቃለሁ ። ይሄን ይወዳል መርጊያው!... እማኞች መቁጠር አለብኝ ። አንዷ አንቺ ትሆኛለሽ!” አለና ጣቱን ወደ ሴትዮዋ ቀሰረ ። “ሌላ... ሌላ ...” ብሎ ወደበሩ ወጣ ሲል በአስፈሪው አነጋገሩ ስጋት የገባቸው አባ እንቀርሻው ጠረጴዛው ላይ የነበረውን ሁለት ብርና ዶሴአቸውን ይዘው ሹልክ ብለው ወጡ ። በጥድፊያ ...

በርቱዕ አንደበቱ ተጠቅሞና በጥራዝ—ነጠቅ ቃላት ባለጉዳዩን ከቤቱ አስደንብሮ ለማባረር የቻለው ራፖር ፀሐፊ እየፈገገ ሰባራ መነፅሩን አወለቀና ወንበሩን ያዘ ፤ ወደ አዲ፱

ባለጉዳይ ፊቱን አዞሮ ።

* * *

ጥልቅ ሃሳብ የገባቸው አባ እንቀርሻው አለ አግባብ የሄደባቸው አንድ ብር በቁጭት አብሰለሰላቸው ። ቀጥለው ምን ማድረግ እንዳለባቸው እያሰላሰሉ የየጁ አውራጃ ፖሊስ አዛዥ ቢሮ ወደሚገኝበት ግቢ አዘገሙ ።

"ይኸን ሁሉ ወረቀት ይዤ ወደ አዛዡ ቀርቤ ፣ በቃሌ ጭምር ባስረዳ አይቀበሉኝ ይሆን? መከራ በልቼ ያሳደግኳት እንዷን ምርኩዜ ከብሯ ተደፍሮ ስትሞትና ያለቀባሪ ስትቀር! እኔም ያለ ጧሪ ስቀር ዳኛ የለም ባገሩ?" እያሉ ራሳቸውን አጥብቀው ይጠይቃሉ ።

ወደ ፖሊስ አዛዡ ቢሮ ሲያመሩ ሸንጡ ላይ ሸጉጥ ያገነደረ ረዥም ደረቱ—ሰፊ ፖሊስ ገላመጣቸው ። ችግራቸውን ሊያስረዱት ቢሞክሩም ሊያደምጣቸው ፈቃደኛ አልሆነም ፣ ከልክሎ ደግሞ አልከለከላቸውም ። እጅ እጃቸውን ያያል ። ምንም የማይወጣቸው መናጢ ድሃ መሆናቸውን ሲያውቅ ግን ተጠይፏቸው ከአጠገባቸው ዘወር አለ ።

አባ እንቀርሻው ጠደፍ—ጠደፍ እያሉ ወደ ፖሊስ አዛዡ ቢሮ ተጠጉ ። ዘንጋቸውን አስቀመጡ ። የነተበ ጋቢያቸውን በባለ—ጉዳይ ደንብ አጣፍተው በልበናቸው ፈጣሪያቸውን ተማፀኑ ። የቢሮውን በር ገፋ አድርገው ገቡና ለጥ ብለው ወለሉን ሳሙት ። በፍርሃት የሚብረከረከው ጉልበታቸው ሊከዳቸው ተቃረበ ።

ከፊት ለፊታቸው ፊቱን የሐምሌ ደመና አስመስሎ የሚመለከታቸው የፖሊስ አዛዡ ሻለቃ ደግሞ በአግራሞት አስተዋላቸው ። ከአባ እንቀርሻው ዓይነት ጎስቋላ ሰው ጋር በቢሮው ሲገናኝ የመጀመሪያ የሆነበት ይመስላል ። ከላይ እስከ ታች መዘናቸው ። ያላበውን ማጅራቱን በመሃረቡ እየጠራረገ ሲቃኛቸው — አባ እንቀርሻው እጆቻቸውን የኋሊት አጣምረው አቀረቀሩ ።

"ምን ነበር?" አለ ሻለቃው ግራ እጁን አገጩ ላይ አስደግፎ ። ግራ እጁ ጣቶች ላይ የተሰኩት የወርቅ ቀለበቶች ዓይን ይስባሉ ።

በአክብሮትና በፍርሃት መላ ሰውነታቸው የታመሰባቸው ባለ—ጉዳይ አሮጌ ጋቢያቸውን ገለጥለጥ አድርገው ከብብታቸው ሥር ዶሴአቸውን መዘው አቀበሉት ። ክላሠሩ አዲስ ነው ። ወረቀቶቹ ግን በላቦት ጠቁረዋል ። ከመላሸቃቸው የተነሳም ሶስት — አራቱ እንደ አነባብሮ የተጣበቁ በመሆናቸው ማላቀቁ ፈተና ነው ።

ፖሊስ አዛዡ የተቀበለውን ዶሴ ገለጥ ሲያደርግ ፣ የሆነ ጠረን አፍንጫውን ሳይወጋው አልቀረም ፣ ክፉኛ አነጠሰው። መሃረቡን አውጥቶ ፊቱ ላይ እያራገበና እየተጠየፈ በሁለት ጣቶቹ ገለጥለጥ አደረገው ፣ የሚያነብ ለመምሰል ያክል። ከዚያም ቀና ብሎ አያቸውና "ምን ነበር?" አላቸው—እንደገና።

"አዩ ጌታዬ ! ምኑ ተነግሮ ! ...ነገሬ ብርቱ ነው" አሉትና ዝም አሉ ።

ክላሰሩን አጥፎ ከፊት ለፊቱ ገፋ በማድረግ "ግዜ የለኝም ። ጉዳይዎን ባጭሩ ይግለፁልኝ!" አላቸው ።

"ክስ ነው ።"

"ማንን ነው የከሰሱ? ለምን?"

"አየ ጌታየ! ዶሴየ ይናገረው ! እኔ ሳወራዎ ውዬ ፣ ሳወራዎ ባድር የሚያልቅ አይደለም" አሉት አባ እንቀርሻው — በደፈናው ። ያ ራፖር ፀሐፊ ያነሳባቸውን የአፍ—እልፊት እንዳይደግሙ ፈርተዋል ። "ተበደልሁ ፣ ፍትህ አጣሁ ፣ የድሃ ብሶትና እንባ ለባለ አዱኛና ለሹም የገለባ ያህል እንኳ የሚከብድ አልሆነም ..." እያሉ የልባቸውን ያህል ካልተና ገሩ ክሳቸው ሰሚ እንደማያገኝ ቢያውቁም ፣ ሊያፈልቁት አልቻሉም ።

"ይህን ዶሴ ገና አንብቤ..." አላቸው ሻለቃው ዶሴአቸ ውን በጥላቻ ዓይን እየተመለከተው ፣ "ጉዳይዎን እንድረዳ ልዎ ካሰቡ የማይሆን ነው ። ግዜ የለኝም ብየዎታለሁ' እኮ !"

"ረጋ ብለው ያንብቡታ! እኔ ከታዛ ሆኜ እጠብቃለሁ።"

"እንዲያማ አይሆንም! ሌላ ቀን ይዘውት ብቅ ይበሉ !" ብሎ ክላሰሩን ገፋላቸው ።

አባ እንቀርሻው ለጥ ብለው እጅ ነሱና "መቼ ልምጣ?" አሉት ።

ነገ...ከነገወዲያ...ሳምንት...የዛሬ ወር...ማለቂያ የሌ ለው ቀጠሮ ።

* * *

አባ እንቀርሻው የፖሊስ ጣቢያውን የውጭ በር አን ቀው ቀሩ ። ወደ ውስጥ እንኳ የሚያስገባቸው ሳያገኙ ውሎአቸውም ሆነ አዳራቸው እዚያው ሆነ ።

ሲጀምራቸው አላወቁትም ። እንኳን እሳቸው ሌላውም ልብ ያለው ከብዙ ግዜ በኋላ ነበር ። አባ እንቀርሻው ወፈፍ



አደረጋቸው ። ከጋቢያቸው በቀር ልብሳቸውን ጣሉ ። ዶሴያቸውን ግን ከደረታቸው አይለዩም ።

"አባቴ...ስምዎ ማነው?" ይሏቸዋል የሚያውቋቸው ፣ ሳቅ ሲያምራቸው ።

"ስሚ?" ይሉና አባ እንቀርሻው "አምና !" በማለት ማንነታቸውን ይገልፃሉ ።

"ያባትዎስ ስም?"

"አቻምና!"

ክፉ ቃል አይወጣቸውም ። በእጫዋችነታቸው ትልቅ—ትንሹ ወደዳቸው ። ሳንቲም ሆነ ፍርፋሪ በአሮጌ ጋቢያቸው እየተቀበሉ የመንገድ ዳር ዚቀኛ ሆኑ ።

"ጎጆ አለዎ አባቴ?"

"እንዴታ! ሰማይ ጣራዬ ፣ ፈረስ መግሪያ ግድግዳዬ!"

"ሚስትዎ ማን ትባላለች ?"

"ዘለቀች ፣ ገበያ ሄዳብኝ ሳትመለስ ቀረች ።"

"ልጅዎስ?"

"ፈጠነች!...ፈጠነች!" ሲሉ ይጠሩና "አረፍ በሉዋ... ቡና ታፈላለች" በማለት የከበቡዋቸውን ያስቃሉ ። መልሶቻ ቸው ምንጊዜም አጫዋቾች ናቸው ።

"አባት ምን ይበላሉ?"

"እንጀት!"

"ምን ይጠጣሉ?"

"ሀሞት!"

"እስቲ ያንጉራጉሩልን!..."

"ምን ከፋኝ!" ይሉና በሸካራ ድምፃቸው

“አቻምና አምናን ወልዶ
አምና ሚስት አገባ
ዘለቀች...ዘለቀች...ዘለቀች
ዋይ! ...ዋይ! ...ዋይ!...
ፈጠነች...ፈጠነች...ፈጠነች

እህህ···አሸሽ ገዳሜ!” እያሉ እንደ እስከስታ ይሞክራቸዋል ። ዜማቸው ሁልጊዜም አንዲት ናት — ሙሾ ብጤ ። ከዚያች በቀር ሌላ ግጥም የላቸውም ።

“እህህ! እ! ...እ! እ...” ይላሉ አልፎ ።

“አባቴ ለምን ያቃስታሉ?”

“ተወጋቼ ።”

“በምን?”

“በእንካሴ! ...እንካሴ ፡ ውላሴ ... እንካሴ ፡ ውላሴ ... እንካሴ ፡ ውላሴ...” ይላሉ ለብዙ ደቂቃዎች ያለማቋረጥ ።

ይህኔ የከበቧቸው ህፃናት በአባ እንቀርሻው ዙሪያ ጡብ...ጡብ እያሉ ይቀበሏቸዋል ። “እንካሴ ፡ ውላሴ...እንካሴ ፡ ውላሴ...እንካሴ ፡ ውላሴ...” ከመሀላቸው አንደኛው በእንካ ሳው እግሩ መሬት ቢነካ ወይ ቢወድቅ “እስክትወጣ ነብሴ!” ሲሉ ያጨበጭቡና “እንካሴ ፡ ውላሴ...እንካሴ ፡ ውላሴ...” ይቀጥላሉ ።

አባ እንቀርሻው እንዲህ እንዲህ እያሉ የመንደር ልጆች አጫዋች ሆነው ኖረው አንድ ቀን ማለዳ ላይ ጋቢያቸውን አስጥተው ከሚቀምሉበት ቆሻሻ መጣያ አጠገብ ዶሴአቸውን እንደተንተራሱ አሸለቡ ፡ እስከወዲያኛው ።

ለተስፋሁን አበራ (መምህ

1982—ወልዲያ



# የማከያው ጥያቄ

ማከያው የእድር ለፋፊ ነው ። በወልዲያ ከተማ እሱን የማያውቅ ማንም የለም። መሬት ሊነካ ጥቂት የቀረው ረዥም የፖሊስ ካፖርት ለብሶ አጭር ወፍራም የብሳና ብትር ይይዛል። ጡሩንባውንም ከእጁ አይለያትም። ከአባቱ የወረሳት ይቺው ጡሩንባ ለረዥም ዘመን አብራው ኖራለች።

የእለት ጉርሱን የአመት ልብሱን የሚችለው የእድሩ አባል ወይም ታገሬው ሰው አንዱ ወይ ሲሞት ወይ የዘመድ ሞት ሲረዳ ወፍ ውሀ ሳይቀምስ ከመኝታው ተነስቶ አንዲትም የከተማዋ መንገድ ሳትቀረው እየተዟዟረ ከለፈፈ በኋላ በሚያገኛት ሁለት ብርና በሽቀላ ነው። ሸክም ያነሳል፣ እንጨት ይፈልጣል፣ ይላላካል፣ ስራው ብዙ ነው።

በለስ ሲቀናው በተከታታይ ስራ ያገኛል። አመዳም እድሉ የባሰውን ስትገረጣ ደግሞ ወሩን በሙሉ ድፍን ብሎበት ይከርማል። ሚስት አለችው፣ አረጋሽ የሚሏት። ከአረጋሽ የወለዳት አንዲት የአራት አመት ልጅም አለችው። ከለመኗት የቆነጠሩላት የምታክል ይቺው ልጁን ‘ሆዴ!’ ይላታል። መንደርተኛውም ለምዶለት በዚያው ነው የሚጠራት።

የሚያገኛት ገቢ የጎጆውን ቀዳዳ አልደፍንለት ብሎ መከራውን ያያል። አረጋሽም ታግዛዋለች፣ የሰፈሩን ጠላ ኮማሪዎች ቂጣ በመጋገር። ገቢም ግን የሚያወላዳ አይደለም። ከወረቱ ስንቁ የላቀ አይነች ነው። ሌሊቱን ቀኑንም ባጉታ

የምታገኛት ሶስት ብርና ሁለት ቁራሽ የአይንሽ ይፍሰስ መጠቃ ነው። ለዚያውም ስንት ደጅ ጠንታ!

ማከያው ግን የሱን ለሱ ትቶ፣ የወለደ ይፍረደኝ ሆኖበት የሆዴ አሳብ ይጠናበታል ። ሆዴ አንጀቷ ታጥፎ፣ ላይዋ ላይ ያለቀ ዝተት የመሰለ ጥብቆዋን ለብሳ፣ አይን አሯም፣ ንፍጧም፣ ለሀጯም የዝንብ ነፍጠኛ እያጋፈረ ፍዝዝ ድንግዝ ብላ ሲመለከታት ሆዱ ይላወሳል።

ንፍጧን ጠርጎ፣ ፊቷንና እግሮቿን አባብሶ አጥቦ ደጋግሞ ይስማታል። ግንባሯን፣ ጉንጯን የእጆቿን መዳፍ ሁሉ እያገላበጠ ይስማል። ጥብቅ አድርጎ ያቅፋታል። ጭኑ ላይ አስቀምጦ ሆዷን እየኮለኮለ ሊያሳስቃት ይሞክራል። ለቅፅበት ፈገግታዋ እንደ ትል እሳት ቦግ ብሎ እልም ይላል። በስጋትና በፍርሀት ትዋጣለች። ያኔ እንባው ይመጣል።...

እና ኑሮአቸው ይኸው ነው፣ ምንጊዜም። ማከያውም ሆነ አረጋሽ አፋቸውን ሳይሸሩ ከቤት ይወጣሉ። የቀንኛውም ቢሆን የማታው እንደተገኘ የሚጐርስ እንጂ ስሙ አለ ብር አድሩስ አይጠራም።

ጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ወታደር የነበረ የአቶ ሺበሺ ትልቅ ልጅ ጦር ግንባር ወድቆ ለአድርተኞች በመለፈፍ ሁለት ብር ካገኘ ወዲህ ሌላ አላጋጠመውም። ድፍን ሳምንቱ። በወልዲያ ከተማ የጥቅምት ወር ብርድ የዋዛ አይደለምና አረጋሽም ስራ ፈታለች። ወሩ ከገባ ጀምሮ የጎጆአቸው ውሎና አዳር ትልቅ ፈተና ሆኖባቸዋል። ከመቸውም የከፋ።

አዳጎ አካባቢ አንድ የዝሀ ነጋዴ እህት ሞታለች ተብሎ



ቤተሰቦቹ በሀዘን ላይ መሆናቸውን ስለሚያውቅ ወደዚያው አዘገመ፣ አድርተኛው ወደ ሀዘን ቤቱ ከሚወስደው ምግብ ትርፍራፊ ለማግኘት።....

እንደደረሰም ጎንበስ ብሎ ድንኳኑ ውስጥ ገብቶ ጥግ ላይ ከሚገኘው አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀመጠ። አጠገቡ የነበሩ ሰዎች የጦፈ ክርክር ይዘዋል። የሟቹ ቤተሰቦች በተነጠፈው ፍራሽ ላይ ተቀምጠው በሀዘን ይወዛወዛሉ።

ማከያው በሁለት እጆቹ አገጩን ደግፎ ዙሪያ ገባውን ይማትራል። ጠላ የሞላ ማንቆርቆሪያ ይዘው በድንኳኑ ውስጥ የሚዘዋወሩት አስተናጋጆች አላዩትም። ቢያዩትም ቁብ አላሉትም። አንዲት ስንጥር ከወለሉ አንስቶ አፈሩን መጫር ጀመረ።

በአንድ እጁ ማንቆርቆሪያ፣ በሌላ እጁ መጠጫ ብርጭቆዎች የያዘው የሰፈሩ የሳር ፍራሽ ሰፊ፣ አብጤ፣ ወደ ማከያው ተጠጋና "ይቺን ዥው አድርግና ውልቅ!" አለው የጉሽ ጠላ በብርጭቆ እየቀዳላት።

ማከያው ቀና ብሎ ተመለከተውና አቀረቀረ። የፍራሽ ሰፊው አነጋገር ትርጉም አልገባ አለው።...

በርካታ አድርተኞች እንጀራ በሰፌድና በትሪ፣ ወጥ በድስትና በስክ ሰሀን ይዘው ወደ ደንኳኑ መግባት እንደጀመሩና የሰው መበራከትን እንደተመለከቱ የነጋዴው ባለቤት ለቅሶ ጀመሩ፣ ደፋ ቀና እያሉ።

"የኔ ቀብራራ
...ቀብራራዬ!
የኔ ቅምጥል

…ቅምጥሌ!

ገንዘብ አፈሩ!

እስከነ ክብሩ!

ተነ ማእረጉ!

ዋይ!…ዋይ!…ዋይ!”

በሰለለ ድምፃቸው አጠገባቸው የተቀመጡት ሀዘንተኞችም ያልጎመጉማሉ። በጋቢያቸው ጫፍ የጨመቋቸው አይኖቻቸውን ይጠርጋሉ። አብዛኞቹ ደጋግመው ይናፈጣሉ።

የሟቹ ባለቤት የሀዘን እንጉርጉሮአቸውን ሲቀጥሉ ማከያው አላስቻለውም ። “እንዴ ! ‘አይገባም!… ተዉ!’ የሚላቸው ሰው የለም?” በሚል ስሜት ተቁነጠነጠ። ወደ ሟቹ ቤተሰቦች ጠጋ ብሎ ለቅሶአቸውን እንዲያቆሙ፣ በባህል የተለመደውን ግሳጼ ሊያስተላልፍ ፈልጎ ከመቀመጫው ብድግ ከማለቱ ፍራሽ ሰፊው “ጥጋበኛ! ጠላህን ጨልጥ! ብርጭቆውን ልወስደው ነው። በአንድ ትንፋሽ! ከዚያም ወደ ቤትህ!” አለው አመልካች ጣቱን ወደ ማከያውና ወደ ጠላ ብርጭቆው እየቀሰረ።

ደንገጥ ብሎ “እረ እኔ ላስተዛዝናቸው ብዬ እንጂ ሌላም አይደለም!” ሲል ማከያው ለስለስ ባለ አነጋገር መለሰለት።

“እንግዲህ አርፈህ ቁጭ በል! አንተ መለፈፍ እንጂ ማስተዛዘን ላይ ምን አገባህ? እረፍ!”

ማከያው ሀፍረት እያሽማቀቀው ተመልሶ ተቀመጠ። የፍራሽ ሰፊው አባባል ይበልጥ ከነከነው። በተለይም አጠገቡ ያሉት ሰዎች ምልልሳቸውን ስላደመጡበት ተሸማቀቀ። “ምን በደልኩት የሚያዋርደኝ!?” አለ ለራሱ። በድህነቱ፣በእርዛቱ



ተማረረ ። ማሰብ ጀመረ ፡ ውል ያለው ሀሳብ ባይሆንም ።…

በሀሳብ ሲብሰለሰል በግራው በኩል የሚያናግሩትን አዛውንት እንኳ ልብ አላላቸውም ። ምሰሶው ላይ ተሰቅሎ ብርሀን ከሚፈነጥቀው ፋኖስ ላይ አይኖቹን ተክሎ ያሰላስላል።

“እስቲ አሁን ምን አገባው? እሱስ እንደኔ ለቅልውጥ አይደል የመጣው! ቅልውጥ ፀያፍ የሚሆነው አመል ሲሆን ነው እንጂ ፡ ለድሀ ምን ያስነውርበታል ? ምንስ በደልኩት?

ብቻውን ማውራቱን ቀጠለ። ግንባሩ ላይ ላብ ችፍፍ ብሏል ። በአደባባይ የተዋረደ ያክል ተሰምቶታል ፡

“እኔም ቆሎ ቢያርብኝ፣ እሱም ቢያርበት እንጂ የሞቀ ጎጆ ቢኖረንማ ሁላችንስ መች እዚህ እንደርስ ነበር? የደንቡን አዝነን በተመለስን! ለመሆኑ ምን በደልሁት?… እስራ ዘጠኝ አመት ለእድሬ አላገለገልኩም?…”

የመጣበትን እንባ ለመመለስ አንዲት የተጣጣፈችና የቆሸሸች የቀሚስ ቁራጭ ከካፖርቱ የውስጥ ኪስ አውጥቶ አይኖቹን ጠራረገ። የጠላ ብርጭቆውን አነሳና ተጎነጨ። መልሶ አስቀመጣት።

ፍራሽ ሰፊው ከንፈሩን እየነከሰበት ማከያው እግር ስር የነበረችውን ብርጭቆ አነሳና የነበራትን ጠላ ደፍቶ “ጠላ ቤት አደረግከው?” አለው በግልምጫ።

ማከያው የባሰውን ሀሳብ ገባው። በፍራሽ ሰፊው አያያዝ ለአረጋሽና ለሆዱ ይዞላቸው ሊሄድ ያሰበውን ቅራፊ ፍርፋሪ ሊከለክለው እንደሚችል ታየው። ጭንቀት አደረበት። አብዛኛውን ጊዜ ከሀዘን ቤት፣ ከሰርግ ቤት፣ ከድግስ…የ

ትርፍራፊ አለቆችን እያስፈቀደ በትልቅ ፕላስቲክ ከረጢት ሞልቶ ይሄዳል ። ያንን ትራፊ ትርፍራፊ በልተው ፡ አረጋሽ የትራፊውን ትርፍራፊ በጥንቃቄ ካስቀመጠች በኋላ ቡና ታፈላለች ። የጠላ ቂጣ ቁርስ ታቀርባለች ። በእንዲህ አይነቱ ምሽት በዚያች ደሳሳ ጎጆአቸው ደስታ ይሰፍናል ። ባልና ሚስቱ "ተመስጌን!" በማለት ዘና ይላሉ ፡ እንቅልፍ እስኪወስዳቸው ወይም የአንድ አምሳል አንድ አካል ተፈጥሮ አዊ ግዴታቸውን መፈፀም እስኪጀምሩ ድረስ ።

የፍራሽ ሰፊው ሁኔታ ግን በጣም አስግቶታል ። ሆን ብሎ በሚፈጥርበት መሰናከል ከዚህ የሀዘን ድንኳን ተስፋ የጣለበትን ትርፍራፊ ካጣ የአረጋሽና የሆዴ ሁኔታ ታየው። ረሀብ አንጀታቸውን አጥፎ፣ አፋቸውን ሸብቦ በጎጆአቸው የሚያንዣብበውን የሀዘን ድባብ ላለማየት ወሰነ። ከፍራሽ ሰፊው ቅይታ ተሰውሮ ፡ ትልቅ ሳፋ ታቅፈው ትርፍራፊ ወደሚሰበስቡት አሮጊት የሚደርስበትን መንገድ ቀየሰ ።

ከመቀመጫው ተነስቶ ጥግ ጥጉን አድርጎ ወደ አሮጊቷ ተጠጋና "እማማ እርጎየ! ለሆዴ የሚሆን እስቲ …ትንሽ ትርፍራፊ ብቤ!…" በብትሩ መሬቱን እየጫጫረ ጠየቃቸው።

"ማነህ? ማከያው! አየ ግዜ!…ዋ! ድሮ አባትህ የናጠጠ ነጋዴ ነበር ። ምን እንደነካው ሳይታወቅ አይምሮው ውሉን ሳተ። ከስንት እመም በኋላ ተሽሎት የእድር ለፋፊ ሆነ፤ እዚችው ወልዲያ፣ እዚችው አዳጎ። ታዲያ በጥጋቡ ግዜ አንገት አልፈጠረለቱም ነበር አሉ። የአባት ሀጢያት ለልጅ አልፎ ይኸው አንተኑ ይቀጣሀል ጌታ!…" ብለው ከንፈራቸ



ውን መጠጡ ። አሮጊቷ ትልበታቸው እየተንቀጠቀጠ ተነሱና አጠገባቸው ካለው የእንጀራ ቁልል ሁለቱን አጣጥፈው ፕላስቲክ ከረጢቱ ውስጥ አደረጉለት ። ሳፋው ላይ ከተቀለለው ትርፍራፊም በሁለት እጆቻቸው እያፈሱ ጨመሩለት ።

በፕላስቲክ የተጠቀለለውን ምግብ በግራ እጁ አቅፎ፣ አጭር ወፍራም ብትሩን በቀኝ እጁ ጨብጦ ፍራሽ ሰፊውን በአይኖቹ እየማተረ እየተጣደፈ ሹልክ አለ ። ከድንኳኑ መግቢያ በግራ በኩል የተኮለኮሉትን በርካታ ጎስቋሎች በፍጥነት አለፋቸው ፥ መሀል ለመሀል አቋርጦ ።

"ቁም!..ሌባ!" የሚል ድምፅ ጆሮው ላይ ጥልቅ ሲል በድንጋጤ ዞሮ አጭር ወፍራም ብትሩን አቀና። ፊት ለፊቱ የተገተረው ፍራሽ ሰፊው ነበር።

"አንተ ባለጌ! እንጀራ ሰረቅህ አይደል?" አለና ፍራሽ ሰፊው አፈጠጠበት የብረት ከዘራውን እየነቀነቀ ።

"ወንድሜዋ…ምን በድየህ! ምን የሚሉት ቂም ነበረ ብህ?" አለ ማከያው፥ በማሳዘን ቅላፄ። ብዙ ቢያስብና ቢብሰለሰልም ፍራሽ ሰፊው እሱን ለመጥላት ያለውን መንስኤ ለማወቅ አልቻለም። የፍራሽ ሰፊው አማት ከሁለት ወር በፊት ሞተዋል። ይህን ሞታቸውን ለእድርተኞች ለፍፎለት የደንቡም ተከፍሎታል። እሱ ራሱ እንኳ ከዚያች ከተከፈለችው ሁለት ብር ፥ የሀምሳ ሳንቲም ጠላ ገዝቶ አስተዛዝኖታል። ከአረጋሽና ከሆዴ ተለይቶ አንድ ሌሊት አብሮት አድሯል። በሶስተኛው ቀንም የሀዘን ድንኳን ሲፈርስ ፡ ምንም ግዴታ ሳይኖርበት ፥ ከተለያዩ ቤቶች በትውስት የመጡ እቃዎችን አንጉዞለታል ።

"ደግሞ ምን በደልኩህ ትላለህ? የሰው መሳቂያ አላደረግከኝም?" አለው አብጤ ፡ ፍራሽ ሰፊው ።

"እንዴት አድርጌ?"

"እማቴ የሞቱ ጊዜ መላ ከተማዋን እየተዘዋወርክ መለፈፍ ሲገባህ በነግራዝማች አበራና በቆሻሻ መጣያው ግድም ዞር ዞር ብለህ በመመለስህ እድርተኞቹ ሁሉ ሳይሰሙ ቀሩ ። የመጣው ሰው በጣም ጥቂት ነበር! እ?...ይህ በደል አይደለም ?"

"ኧረ ተው፣ አለ ስራዬ ስራ አተሰጠኝ!?"

"ዝም በል!" አለና ፍራሽ ሰፊው የብረት ከዘራውን ጫፍ ማከያው አይኖች ላይ አድርሶ መለሰው። ቀጠለና "ሰው ጋር እንደማልወዳጅ፣ አገር እንደማይወደኝ፣ ለሰው መጥፎ እንደሆንኩ ተደርጌ የተቆጠርኩት ባንተ ምክንያት ነው። እድሩ የሰጠኝ ደበስም ትንሽ ነው። ምን ይህ ብቻ!? ሶስት ቀን ሙሉ በሀዘን መኮራመቴ እንዳይበቃኝ 'አልሰማንም! ማን ነገሮን?' እያለ በየቀኑ የሚመጣውን እድርተኛ ስቀበል ስራ አላስፈታኸኝም? እ? ከዚህ በላይ ምን ልታደርገኝ ትፈልጋለህ? አህያ ካላረድክብኝ ነው?"

ፍራሽ ሰፊው የብረት ከዘራውን ደጋግሞ ነቀነቀ ማከያውን ላይና ታች እየገላመጠው። "ስራየም አይደል ወንድሜ! በህግ አምላክ!..." አለና ማከያው ራመድ ሲል ፍራሽ ሰፊው የካፖርቱን ክሳድ ጨምድዶ አስቆመው።

"ልብ አድርግ! ዋ! ሌላም የሰማሁብህ ጉድ አለ። መቃብርህን እየማስክ ነው። ተጠንቀቅ!!" አለና ፍራሽ ሰፊው ንግግሩን አንጠልጥሎ ተወው ።



የፍራሽ ሰፊው ዛቻ ማከያውን ጤና ነሳው። ይህን ያህል ያስፎከረውና ተፈፀመብኝ የሚለው በደል እስከዚህ የሚያናክስ ሆኖ አላገኘውም ። ሌላ ምስጢር ቢኖር ነው እያለ የሆዱን በሆዱ ይዞ ጥቂት ቀናት አሳለፈ።

አንድ ቀን ከቀትር በኋላ ፡ ማከያው በለስ ቀንቶት እንጨት ፈለጣ አገኘ ። በፊቱና በማጅራቱ የሚንቀረቀረውን ላቡን እየጠረገ የቀረበለትን ግንድ ሲሸነሽን ውሎ ማታ ገደማ ሳንቲሙን በእጁ ሲያስገባ ውሻ በቁልቁለት የማይጎትተው ገብስ እንጀራ ከወፍራም ሽሮ ጋር ተጨማሪ ተሰጥቶት ያን በጣሳ ውሀ ካወራረደ በኋላ ፈጣሪውንና አሰሪውን አመስግኖ ወጣ።

ምሽት ላይ ከአረቄ ኮማሪቷ ከየዋግነሽ ቤት ጎራ ብሎ በመዝናናት ላይ ሳለ የልብ ወዳጁ አባ ምትኩ ሪዛቸውን እያፍተለተሉ ገብተው ከጎኑ አረፍ አሉ። እውቅ ሸማኔ ናቸው። ጥሩ ገቢም አላቸው። ታዲያ እግራቸውን ከሸማኔ ጉድጓዳቸው እያውጡ እንጂ ካወጡ እግር ተወርች አስሮ የሚመልሳቸው ጎበዝ ይፈልጋሉ። አላፊ አግዳሚውን ይጎትታሉ፣ ይጋብዛሉ። ጠላው፣ ጠጁ፣ ካቲካላው፣...ምኑም አይቀታሉ፣ ይጋብዛሉ። ጠላው፣ ጠጁ፣ ካቲካላው፣...ምኑም አይቀ

አባ ምትኩ ሌላም መስህብ አላቸው። ውሎዋቸው ከመንደር ሴቶች ጋር በመሆኑ ይመስላል፣ ወሬ አያመልጣቸውም። በወልዲያ ከተማ ተደረገ፣ ተወራ የተባለው ቀርቶ መንዝና ገመገም ተሻግሮ የሚመጣላቸውን ትኩስ ዜና ለመስ

ማት የሚከባቸው ሰው ብዙ ነው።

"እህሳ፣ ማከያው ደህና አመሸህ?" አሉት፣ ዘንጋቸውን ከጎናቸው እያስደገፉ። ግሳት ግሳት ይላቸዋል።

"ይክበር ይመስገን፣ አባ ምትኩ" አላቸው ማከያው ብድግ ብሎ እጅ በመንሳት።

"የዋግነሽ!" ድምፃቸው ከጣራ በላይ ነው።

"አቤት አባ ምትኩ" ስትል ከጓዳ ብቅ አለች።" ደህና አመሹ?"

"ካቴሽ እንዴት ነው? ሆዴን ነፍቶኛል" እያሏት እጃቸውን በጋቢያቸው ስር ልከው ሆዳቸውን ቸብ ቸብ አደረጉ ። ተቆዝሯል ።

"ትኩስ ነው" አለቻቸው የዋግነሽ ፡ ክፍሉ መሀል በተገተረች አንዲት አንካሳ ጠረጴዛ ላይ ተደፍተው ከተኮለኮሉት መለኪያዎች አንዱን እያነሳች ።

"የአበዛሽ ጠጅ በተሃ ሆነብኝ ። ቀደም ሲል ደግሞ ጉሽ ጠላ ቀምሼ ነበር ቀብትቶኝ ጎንበስ ቀና ማለት እንኳ አቃተኝ" አሉ አባ ምትኩ ። ጋን ጋን ይሸታሉ ። ምላሳቸውም እንደመኮላተፍ ብሏል ። "በብርሌ አድርጊው ።" የዋግነሽ ብርላዋን ሞልታ ገጭ አደረገችላቸው ።

"ለማከያውም ቅጂ ። አንቺም ያዥ" አሏት አባ ምትኩ፣ የተሞላላቸውን በአንድ ትንፋሽ አጋብተው ድጋሚ እያስቀዱ ።

"አዬ አባ መስጠት!" ሲል አሞካሻቸው ማከያው ።

"አባ ዝናብ በላቸው እንጂ!" አለች ከማሪትዋም ።



"በየገቡበት ሳያርከፈክፉ አይወጡ ።"

አባ ምትኩ ኩራት ኩራት አላቸው ። ደጋገሙ ። የተጋባዦቻቸውም መለኪያዎች የሚጋቡት በቅልጥፍና ነበርና ሌላ ቀረበላቸው ።

"ምናባቱ!" አሉ አባ ምትኩ ፣ "ድህነት ውሉን አይስትም ። ሲያገኙ አብሮ መብላትን ፣ መጠጣትን ፣ መደሰትን ፣ ሲያጡም አንጀት አስሮ ማደርን ለምደነዋል ።"

"ብቻ ጤና እንሁን!" አለች የዋግነሽ ፣ ምላሷን እየመጠጠች ።

"አዎ ፣ ዋናው ጤንነት ነው" አለ ማከያውም የበኩሉን ሀሳብ ሲዘነዝር ። "አዱኛ ጤዛ ነው ። ባለው ጊዜ ያላካፈለ ፣ ባጣ ጊዜ ማ ሊደርስለት?"

"አዬ ተወኝ ባክህ! በዛሬ ዘመን ሁሉም በልቼ ልሙት ብሏል ። እንዲህ በጐ በጐውን የሚያስብ የታል ብለህ?" የአባ ምትኩ ቅሬታ ነበር ። "ሰው ለሆዱ ተገዥ ሆኗል ። ጆሮ አይሰማው ፡ አይን አያየው የለ ፣ ብዙ ጉድ እየታዘብኩ ነው" በማለት አባ ምትኩ ለወሬ ምላሳቸውን ሲገሩ ማከያውና የዋግነሽ ጆሮዎቻቸውን ቀሰሩ ።

"በጉድ ዘመን ተፈጥረን..." በማለት ማከያው ለማሚ ማቅ የጀመረውን ሀሳብ ሆን ብሎ አንጠልጥሎ አስቀረው ።

አባ ምትኩ በልባቸው ያመቁትን ለመዘርገፍ ቸኩለዋል። "መቼስ" አሉ ወገቢ ያደረሷትን መለኪያ እንደጨለጡ "ጉድና ጅራት ከወደኋላ እንዲሉ ፡ ፈጣሪ እድሜ ከሰጠን ብዙ ጉድ ወደፊት እንሰማለን ፡ እናያለን ።"

መለኪያቸውን አጋብተው አስቀመጡ። ማከያው ሞላላ ቸው። የራሱንም አንጠፍጥፎ ከሞላ በኋላ "በእኔ ሂሳብ ደግሞ አንድ ብርሌ አምጪ!"አላት የዋግነሽን ። እሷም ወሬው እንዳያመልጣት ተጣድፋ ከመቅፅበት አቀረበች ።

"ሰው ተበላሽቷል" በማለት ጀመሩ አባ ምትኩ ። "ባለፈው ሰሞን አንዲት የወረኢሉ ሴት እየሀ መጥተው እህታቸው ዘንድ አርፈው ነበር ። እና በጨዋታ አንዱን ስንጥል አንዱን ስናንጠለጥል የእድር ነገር ተነሳ ።"

ማከያው ቀና አለ ። የዋግነሽም አሰገገች ።

"ታዲያ እኒያ ሴት ምን አሉኝ መሰላችሁ? 'በቀያችን ነጋ ጠባ ፣ እዚያም እዚህም መርዶ በዛና በመዋጮ ጓዳችን ተራቆተ ፣ የእድር ጥሪታችን ተሟጦ የጎሪጥ እየተያየን ነው' ሲሉኝ 'እንዴት?' አልኳቸው ። መልሳቸው ዘግናኝ ነበር ። 'የእድር ዳኛቸው ኀዘን ደረሰብን ከሚሉት ሰዎች ጋር እየተመሳጠሩ ፣ ያልሞተ ዘመድ ሞተ በማሰኘት ገንዘብ ይቀራመታሉ የሚል ወሬ በድንገት ተናፈሰ ። ደሀ ጉጉ ነው ። እንዴት ልበለው በሚል ፈሊጥ ያለ የሌለ ዘመዱን መግደል አመጣ ። በተለይ ብዚህ በጦርነቱ ፣ ወታደር የነበረ ወንድም ፣ አጎት ፣ አጣሁ የሚለው ሰው ቁጥር እያየለ ሄዶ አይናችን ፈጠጠ!' 'አዬ ሰው!' ብዬ ጆሮዬን በዝሀ ብጣሽ ጠቀጠቅሁ ።"

"ጉድ!ጉድ!" አለች የዋግነሽ ፣ ነገሩ ሰቅጥጧት ።

"እንዲሀ ሆነን አረፍነው?" አለ ማከያውም ተደናግጦ ።



"ኤዲያ!" አሉ አባ ምትኩ ፣ "ለአንተማ ምን ክፋት አለው? በየቀኑ ጡሩምባህን መወልወል ነው ።"

የዋግነሽ ከትከት ብላ ሳቀች ።

"እኛ ዘንዳ እንኳ እንዲያ አይሆንም!" አለ ማከያው። ግን ፍላጎቱን መግታቱ ይሁን ወይም ድርጊቱን መቃወሙ ግልጽ አይደለም።

"ለምን አይሆን?" የአባ ምትኩ ጥርጣሬ ነበር። "በእኛ ሆነ በሌሎቹ ቀበሌዎች ዘንድሮ መርዶ አልበዛም? ከፉ ማሰብ ከፉ ያናግራል አትበሉኝ እንጂ ፣ እኔ አቶ ተገኔን ጠርጥሬዋ ለሁ" ብለው በሹክሹክታ  መለኪያቸውን አነሱ ።

አቶ ተገኔ የቀበሌያቸው የእድር ዳኛ ናቸው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን አመለኛ ሆነዋል በሚል ስሜት ሰፈርተኛው እየራቃቸው ነው ። ውሎዋቸውንና ማምሻቸውን ከማይረቡ ሰዎች ጋር አድርገዋል ። አንዱ ወዳጃቸው እሳት የላሰው ደላላ አራጊ ሲሆን ፣ ሌላው ፍራሽ ሰፊው አብጤ ነው ። አራጊ የማይገባበት ጓዳ ፣ የማያቀባብለው ነገር የለም። በዚህም አድራጎቱ ብዙውን የአገሬውን ሰው አነካክቶ በየደረሰበት እርግማን ቀለቡ ሆኗል ። አብጤም ቀን ቀን የጭድና የጀንያ ፍራሹን ያገላብጥ እንጂ አገር በጨለማ ድባብ ሲሸበብ ፣ የአዳም ልጅ በእንቅልፍ አለም ሲታጀብና ቀየው ፀጥ ረጭ ሲል ወንዝ ያመጣው ግንድ በሚያከለው ክንዱ ቤት እየሰረሰረ እንደሚዘርፍ ሰው ደፍሮ ፊት ለፊት ባይናገረውም ቡና ይጠጣበታል ። በዚህ ላይ ሽማግሌ ያሰለቸ ጠበኛ ነው ። እሱ በሆረበት መሸታ ቤት ሰው በራሱ ጉዳይ ተያይቶ ቢስቅ "በኔ ነው የምትስቀው? ምናባህንስ !.. እኔ ለበኑ!" ብሎ

ለማድያ ይገለገላል ። ድፍረቱንም ፡ ጉልበቱንም ያደለው በመሆኑ እንኳን ያልሞላለት ተደላደልኩ ያለ ባለጠጋም በአይኑ ሙሉ አያየውም።

"ተገኔ የተበላሸው ከአብጤና ከአራጌ ጋር ከገጠመ ወዲህ ነው" አሉ አባ ምትኩ ወደ ገቡበት ፍሬ ሐሳብ በመመለስ ። "አብጤ አማቴ አረፈች ብሎ በያ ሰሞን አስለፍፎህ የእድር ገንዘብ ኪሱ አስገባ ። የመዋጮ እንጀራ ውን አድርቆ አስወቅጦ ሲበላ ከረመ ። አማቱ ከሞተች አስር አመት ያለፈ መሆኑን ከሁነኛ ሰው ሰምቻለሁ ።"

"እኸ!" አለ ማከያው ፡ የሆነ ሐሳብ ብልጭ ብሎለት ። "መርዶ ነጋሪውስ አራጌ አልነበረ?"

"እያልኩህ! ሰው ኑሮ በዘዴ ብሎ የያዘው ይኸው ጉድ ሆኗል ።"

ምሽቱ እየገፋ ሄዶ ጨለማው ሰፍኗል ። የዋግነሽ መጠጡም ፡ እንቅልፉም ከብዷት አስሬ ያፋሽጋታል ። አባ ምትኩና ማከያው ግን ገና እያንቆረቆሩ ነው ።

"ቡና ላፍላ?" አለቻቸው የዋግነሽ ፡ መቀመጡ ቢጨን ቃት ።

"አይ! አይ!" አሏት ሁለቱም ፡ "ካቴሽ ማለፊያ ነው።"

"አንድ ብርሌ ለመንገድ በይን ። ሂሳቡም በእኔው ነው" በማለት አባ ምትኩ በመርፌ ቁልፍ የሰፉትን የእጀ ጠባባቸውን ኪስ በረበሩ ። ማከያው አላግደረደራቸውም ። አስር ብር የዋግነሽን አስጨበጧት ።

"እና ነገ ማለዳ ስራ እ:ታጣም!" አሉት ማከያውን



በክርናቸው ጐሸም አድርገውት እየሳቁ ። ማከያውም ሳቀ ።

"ደሞ ምን መጣ?"

"አራጌ የእናቱን ሞት ሊረዳ ነው" አሉት አባ ምትኩ እየተንከተከቱ ።

"ኧረ ባዛኚቱ!... ጉድ!" አለና ማከያው ጆሮውን ማመን እያዳገተው ። "ማ ነገረዎ?"

"ከነገረኝ ሰው ምን ጉዳይ አለህ?"

"አይ!...እንደው ..." አለ ማከያው በማቅማማት ፤ "ለጫወታው ብዬ እንጂ ... ምን ፋይዳ አለው!"

መለኪያዎቻቸውን በፍጥነት ቁጭ ብድግ ሲያደርጉ ቆይተው ከዋግነሽ ቤት ወጡ።

"አባ ምትኩ" አለ ማከያው ፡ በመንገድ ላይ ሳሉ ፡ "ላምን አልቻልኩም ። ጊዜውን ዘነጋሁት እንጂ ፡ እናቱ እንደሞቱበት ከዚህ ቀደም ራሱ አራጌ አውስቶልኝ ነበር ። ትዝ ይለኛል ፤ ያሁኑ የዋግነሽ ቤት ይሁን ሌላ ቦታ፣ ተገናኝተን እንዲሁ እንደዛሬው ስንጫወት በዚያ በከፋ ዘመን ፡ በረሃቡ ወቅት እናቱ ባቲ መጠለያ ገብተው ሕይወታ ቸው ሲያልፍ እሱ ኩሊነት ይሰራ እንደነበር አውግቶኛል ።"

"እኔም የሰማሁት ይሄንኑ ነው" አሉት አባ ምትኩ ።

በዚሁ ተለያዩ ። ነገሩን እያብላላ ማከያው ብቻውን ወደጐጆው ደፋ ደፋ ማለቱን ቀጠለ ። የዚያ ቀደሙን የፍራሽ ሰፊው የአብጤን ዘለፋና ማስፈራራት ከዚሁ ጉዳይ ጋር አዛመደው ።

ቤቱ ከከተማው ጥቂት ወጣ ይላል ። የመንገዱ ግራና ቀኝ በባሕር ዛፍ ቁጥቋጦ የተጀቦነ ነው ። ገባ ብሎ ከተፀዳዳ

በኋላ ሱሪውን እያጠባበቀ ብቅ ሲል ሁለት ሰዎች ከቅርብ ርቀት ወደ እሱ አቅጣጫ ሲመጡ ተመለከተና አጭር ወፍራም በትሩን አጥብቆ ጨበጠ ። ልቡ ትር ትር አለች ።

"እንደምን አመሸህ ፣ ማከያው?" አሉት አቶ ተገኔ ፣ የእድር ዳኛው ። "ቤትህ ብንሄድ አጣንህ ።"

አብጤ ፍራሽ ሰፌው ፈንጠር ብሎ ቆሟል ።

"ባክህ ችግር ገጥሞናል ።" የአቶ ተገኔ መግቢያ ነበር ።

"ምነው? ደህናም አይደላችሁ እንዴ? ምን እክል ገጠማችሁ ?"

"እባክህ ንጋት ላይ ቶሎ በል!" አሉት አፋቸው እንደመ ተሳሰር እያለ ። "የዚያ የእድርተኛችን... ታውቀው የለ እንዴ? ያ...አራጌ ደላላው! እናቱ ሞተዋል ፤ ቶሎ በል!"

"እንዴት ሞቱ?"

"ምን ያደርግልሃል ? አጥብቀህ ስትጠይቅ አበ ልጅ ያለህ አትመስልም? ከአማሟታቸው ምን አለህ?"

"ኧረ በጉዴ ወጣሁ!" አለ ማከያው እየተልጐመ ጐመ ።

"ወይ ጥጋብ! አንተ ምናለብህ እናቴ! ያገሩ ሰው አንዱን ጠዋት ቀብሮ ሌላውን ማታ እየደገመ የእዝኑ ፍትፍት ላንተ ሰርግ ነው የሆነልህ ... ልብህ አበጠ ! ተበሪዱን ይስጥህ!"

"ምን አርግ ነው የሚሉኝ?" አለና እንደማፍጠጥ ብሎ አቋረጣቸው ።

"ደግሞ ምን ለማድረግ ያምርህ ኖሯል? ድሮውንስ ቢሆን ዝሆንና አውራሪስ አታድን ። እንደ ጋለሞታ መንደር



ለመንደር እያውደለደልህ ፣ ጡሩንባህን እየነፋህ ፣እድሜ ለሙታን ፣ እድሜህን ቀጥል እንጂ!"

"ኧረ ጉዱ!" አለ ማከያው ።

"መድሃኒአለም ለጉድጓድ ይዳርግህ ፣ አቦ!" አሉና ማጅራቱን አንዳች በሚያክል መዳፋቸው ይዘው "የ—ዚ—ያ የ—ደ—ላ—ላ—ው እ—ና—ት ሞ—ተ—ዋ—ል! የአራጌ!" ብለው ሲገፈትሩት ተውተርትሮ ቆመና ፈገግ ብሎ አያቸው ።

"ጥርስህ ይርገፍ! ደግሞ ይስቃል?"

"መቸ ሞቱ?" አለ ማከያው እንደማስተዛዘን ብሎ በሽሙጥ አነጋገር ።

"ሰውየ! ሰይጣን ሰርሃል እንዴ! ጤና የለህም? ትላንት ቢሞቱ ዛሬ ፣ ዘልዝለህ ቋንጣ አታድርጋቸው!" አሉት ኮስተር ብለው ።

"አላልኩም ! አልወጣኝም !"

"በል ወንድሜ!" አሉ አቶ ተገኔ እልህ እየተናነቃ ቸው። "ከእኔ ጋር እንካሰላንትያውን ተወውና ጡር ፍራ! አራጌ እንደ ሰው እድርተኛ ነኝ ብሎ ውጭጭ ከፍሎና የማታ እራት ብቻ ይዞ አይደለም የሚያስተዛዝነው ። ሰው ሞተ ሲባል ቀድሞ ቀብር የሚቆፍረው እሱ ነው። የናቱን መርዶ ነገርለትና እድርተኛው ያስተዛዝነው!"

ማከያው ነገሩ በቀጥታ ገብቶታል ። አይኖቹን አይና ቸው ላይ ተክሎ "አየ ሰው!" አለ በልቡ ። የፍራሽ ሰፌው ዛቻና ማስፈራራት እንቆቅልሹ ተገለጠለት ።

"እድምጠኸኛል ያዘዝኩህን?" አሉና የእድር ዳኛው ማከያውን ገፋ አደረጉት ።

"አላዳምጥም አባ ተገኔ ። ጀር የለኝም!" አለ ማከያው
"አላዳምጥም አባ ተገኔ ጀሮ የለኝም!" አለ ማከያው ብትሩን በጉያው ይዞና በሁለት እጆቹ ሁለት ጆሮዎቹን ጥርቅም አድርጎ ።

"የታዘዝከውን አትሰራም?"

"አላደርገውም!"

"በምን ምክንያት?"

"ሀሰት ነዋ! አራጌ እናት የለውም! ጠንቅቄ አውቃለሁ። ኃጢያት በገዛ እጄ አልሰራም!… ለነብሳችን እንዘን እንጂ አባ ተገኔ! በላይ ቤት መጠየቅ አለ'ኮ"አለና ማከያው ብትሩን ወደ ሰማይ ቀስሮ አንጋጠጠ ።

"እንዴት እናት የለውም?"

† "የለውም ብያለሁ የለውም! አንድ ሰው አንድ እናት ነው ያለው! በኛ ይቅር … ፀያፍ ነው ፣ አባ ተገኔ! እንኳን የአራጌ የየህ ቀደሙ የአብጤም መርዶ ሽፍጥ ነው ። ጅስጢራችሁን በሆነ ቦታ ደርሼበታለሁ ።"

•"እኔ አዝዣለሁ! ባትለፍፍና ይኸ ምስኪን የኀዘኑ ደንብ ቢሰናከልበት ውርድ ከራሴ!" አሉት ። ግን ዛቻ ያዘለ ማስጠንቀቂያቸው ማከያውን ደንገጥ አላደረገውም ።

"የሐሰት ሞት አላውጅም! እድርተኛው ይፍረድብኝ!" አላቸው ማከያው ፍርጥም ብሎ ።

"ነግሬሃለሁ ! ያንተ ሞት እንዳይለፈፍ! ስም አጥፊ!… ቆሽማዳ! ማነህ አንተ የእድርተኞችን ስም የምታጠፋ!" የእድር ዳኛው በስጋትና በጥርጣሬ በግነው የስድብ ናዳቸውን አወረዱበት ።



"በሕግ አምላክ! የሀሰት ሞት ለፋፊ አይደለሁም። ለሁለት ብር ብዬ ማተቤን አልበጥስም። ክርስቲያን ነኝ! ማተቤ ጥብቅ ነው" አለና ማከያው አንገቱ ላይ የዞረውን ክር በጣቶቹ ሳብ ሳብ አደረገው ።

"ቆይ ታገኝታለህ!"

"ምን ሊያደርጉኝ!" አለና ማከያው ጉያው ውስጥ የነበረውን ጡሩንባ አወጣ ። "ጉዳችሁን ነው የምለፍፈው! እኔ ማከያው ነኝ የምሰድበው ፣ የምዋረደው? አገር ይወቅ! በዚህ ጡሩምባ ጉዳችሁን ነው የምለፍፈው!" አለ መላ ሰውነቱ በንዴት እየተንዘፈዘፈ ።

"ሞት ሸቶሃላ! በል ሞክር!"

ፍራሽ ሰፊው ከዚህ መጣ ሳይባል ተቀላቀላቸውና ለነገሩ አዲስ በሚያስመስለው አይነት ስሜት የእድር ዳኛውንም ማከያውንም ቃኛቸው ።

"ታያላችሁ!" አለ ። ማከያው ራመድ ራመድ ብሎ ፊቱን ወደ ፀሐይ መውጫ አድርጎ ጡሩንባውን በረዥሙ ከነፋ በኋል … የወጣው ቃል አልነበረው ። አፋን ጥርቅም አድርጎ ካፈነው ጠንካራ መዳፍ ለመላቀቀ ተጣጣረ ። … ተንፈራገጠ ። አልቲሳካለትም ። ትንፋሽ አጠረው ። ወደቀ።

የእድሩ ዳኛ ጀርባቸውን ሰጥተዋቸው ሲሄዱ ፍራሽ ሰፊው መራራ ፈሳሽ ነገር አፉ ላይ አንጠባጠበበት ። ማከያው ሰመመን ያዘው ። ብዥታ ተጫጫነው ።…

ከዚያ በኋላ የእድር ለፋፊነት ስራውን አልቀጠለበትም። ስለአረጋሽም ሆነ ስለሆዴ እንደወትሮው ማሰቡ ቀረ ።

በዋለበት ውሎ ፣ በመሸበት የሚያድር ባተሌ ወጣው ። ከቀናው የምፅዋት እህል ይቀምሳል ። ካላገኘም አንጀቱ እንደታጠፈ ከደረሰበት ታዛ ጋደም ብሎ ያነጋል ።
ምንም ነገር አይታየውም—ባዶ ቀፎ…በድን አካል ሆነ ።

ልብ ብሎ የሚያዳምጠው ባይኖርም ቀኑን ሙሉ በአዳጐ አካባቢ እየተዘዋወረ አንዲት ነገር ብቻ ይናገራል ። እሷኑ ሲደጋግማት ይውላል ። "ጉዳችሁን ልለፍፍ?" አመልካች ጣቱን አላፊ አግዳሚው ላይ እየቀሰረ ። የማንን ጉድ? የመቼ...? ማንም ቢሆን ምላሽ አላገኘለትም ፣ ለማከያው ጥያቄ ።

የካቲት 1984

# "ወሬ ክማሪው"

ጋዜጣኛው ድንቃለም ሀይለየሱስ ጥቁር ጠላ ፍለጋ በባሻ ወልዴ ችሎት ሰፈር ይዘዋወራል ። የወይዘሮ ባፈሳ ጥቁር ጠላ ደንበኛ ነው ። ወዳጅነትም አፍርተዋል ። ከስራ መልስ ወደ መሺታ ቤታቸው ሄዶ ነበር ። "አልቋል" አሉት ። ስላለቀ ግን አልነበረም ። አርባ አምስት ብር ያህል እዳ ነበረበት ። በተደጋጋሚ እንዲከፍላቸው እየጠየቁት ለትላንት ማታ ሊያመጣላቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር ። ስላልተሳካ ቀርቷል። በአድራጐቱ የተናደዱት ወይዘሮ ባፈሳ 'አልቋል' ያሉት በዚህ ምክንያት ነበር ።

ድንቃለም ጥቁር ጠላ ይወዳል ። የወደደው በሁለት ምክንያቶች ሲሆን ዋናው ምክንያቱ ሌላ መጠጥ ለማዘዝ የገንዘብ አቅም ስላልነበረው ነው ። ከስራ ጓደኞቹ እይታ



እየተደበቀ ነበር ጥቁር ጠላን የጀመረው ፤ ሀሜታቸው እያስፈራው ። የኋላ ኋላ ግን መደበቁን እርግፍ አድርጐ ተወ ። ከቢሮው እንደወጣ በቀጥታ እሱኑ ፍለጋ ሽቅብ ቁልቁል ይላል ። የስራ ጓደኞቹ ሆኑ ሌሎች ቢያገኙትም ግድ አልነበረውም ። እንደ ድሮው ሊዋሻቸው አይፈልግም ። ጥቁር ጠላ ፍለጋ እንደሚዞር ይነግራቸዋል ። ፈገግ ይሉበታል ። እሱም አብሮ ይፈግጋል ።

ከወይዘሮ ባፈሳ ጋር የተዋወቀው በአጋጣሚ ነበር ። አንድ ምሽት የተጠናወተው ሱሱን ለመወጣት ሲቅበዘበዝ እኚህ ቀይ ዳማ ወይዘሮ በጥቁር ጠላ የተሞሉ ጠርሙሶችን ከባልዲ እያወጡ ጠረጴዛ ላይ ሲደረድሩ ተመለከተ ። አላመነታም ።

"ጥቁር ጠላ ይኖርዎታል ?" አንገቱን ብቅ አድርጐ ።

"ያውም አፍ የሚሞላ! ድራፍትን የሚያስንቅ!" አሉት ተኩራርተው ።

"እንዴት ማለት?" እየተቀመጠ ።

"ቀምሶ ማረጋገጥ!" ተሞልተው መደርደሪያው ላይ ከተቀመጡት ጠርሙሶች አንዱን አንስተው በብርጭቆ ቀዱለት ። ከማቅረብ አልፈው ብርጭቆ የሚሞሉት በወይዘሮ ባፈሳ ግምት ፣ ሚዛን ለሚደፉ ሰዎች ነው ።

"ማጨስ ይፈቀዳል?" ሲል ጠየቃቸው ፣ የሚገላበጠው መቀመጫቸውን አፉን ከፍቶ እየተመለከተ ።

"የፈለገ ያምቧለው ! እሱ ሊያጨስ ፣ ራሱ ሊጨስ እኔን ለምን ያስፈቅዳል?" አሉት በመሽኮርመም መልክ ፈገግ ብለው ።

"እርስዎስ ለምን አይጠጡም?" አላቸው ጭውውታቸው የሚቀጥልበትን መንገድ ካውጠነጠነ በኋላ ።

"አብሮኝ ውሎ ስለሚያድር እያንገሸገሸኝ ነዋ!" ብለው ወጣ ያለውን ቦራጫቸው በሁለት እጆቻቸው መታ መታ እያደረጉ በተለያዩ ቅርፆች የተሰሩ አራት የጣት ቀለበቶቻቸውን አሳዩት ። "ራሴ የጠመቅሁትን ጠላ መጠጣት አቃተኝ ። መጠጥ ሲያምረኝ ቢራ ነው የምቀምሰው !" አሉት ። መሸታ ቤታቸው ሁለገብ ነው ፤ ጠጪ እንደየኪሱ ፣ እንደየፍላጐቱ ያሰኘውን እንዲጨብጥ ፣ ያበሻውም የፈረንጁም መጠጥ የሚገኝበት ።

"ታዲያ ምናለ ! ይጠጡዋ! ውስኪም ቢሆን እከፍላለሁ። የትውውቅ ግብዣ ይባላል ።" ሲጋራውን አውጥቶ ለኮሰ ። ለአፍ ያህል እንጂ ምርጫቸው ውስኪ እንደማይሆን ትማምኗል ።

"ውስኪ እንኳ የለኝም ፣ አመሰግንዎታለሁ!" አሉና አመልካች ጣታቸው ላይ ያጠለቁትን የወርቅ ቀለበት ወጣገባ እያደረጉ ተቅለሰለሱ ፤ ሲግደረደሩ ።

• "ቢራ ይያዙዋ !" ከማለቱ ሁለት መዳፋቸውን ጉልበቶቻቸው ላይ አስደግፈው ከቱነሱ በኋላ መቀመጫቸውን ከፍ ዝቅ እያደረጉለት አንድ ጠርሙስ ቢራ ከሳጥን አውጥተው ከፈቱና ተጐነጩ ፤ በቁማቸው ።

"ይጫወቱ!" አሉ ወይዘሮ ባፈሳ ፊት ለፊት ተቀምጠው ።

"አንቱ ለምን ይሉኛል ?" የጨዋታ መክፈቻ በማግኘቱ ደስ አለው ።



"እርስዎስ አንቱ ለምን ይሉኛል?"

"እኔ ሶስት ምክንያቶች አሉኝ ። አንደኛ ከርስዎ በድሜ አልበልጥም ። ሁለተኛ ደግሞ አዲስ ደንበኛ ስለሆንኩ እስክንላመድ ... አለ አይደል ? ሌላው ምክንያቴ ደግሞ ጋዜጠኛ 'አንቱ' ስለማይባል ነው ። ለምን የማቱሳላ እድሜ አይኖረውም! አንተ እንደተባለ ነብሱ ምንጥቅ ትላለች" አላቸው ያለቀችውን ሲጋራ ወለሉ ላይ ጥሎ በጫማው ተረከዝ እየደፈጠጠ ።

"እኔም አንቱ ሲሉኝ አልወድም" ብለውት ፊታቸውን ለአፍታ ኮስተር አደረጉና "ውፍረቴ'ኮ የእድሜ አይደለም ። የምቾትም አልለው ፣ መች ደልቶኝ! ጋን ሳገላብጥ ነው የምኖረው ። እንደውም ደስ የሚለኝ ሰው 'ባፈሳ'! ሲለኝ ነው። አንዳንዶቹማ 'ባፌ! ባፌየ! ባፌና!' ሲሉኝ በጣም እወዳቸዋለሁ ።" በረዥሙ ሳቁ ።

"እኔም 'ባፌ' ልበላ ታዲያ?"

"ደስ ይለኛል!" ብለውት የቢራ ጠርሙሳቸውን ተጐነጩላትና ወደ ላይ ከፍ አድርገው ተመለከቷት ፤ ባዶ መሆኗን ለማመልከት ።

"ጨምሪ ባፌ ፣ እከፍላለሁ ።"

"ያንተን ስም ማን ልበል?" ሌላ ቢራ ጠርሙስ ከፈቱ ።

"ድንቃለም ! የጋዜጣ አዘጋጅ ነኝ ።... ጋዜጠኛ"

"ባፌ ካልከኝ እኔም 'ድንቄ!' ነው የምልህ!" በግራ አይናቸው ጠቀሱት ። ድንቃለምም ጉንተል አደረጋቸው ።

"ቤቱን ዘጋ ላድርገው እንዴ?"

"ደስ ይለኛል ባፌ!" አላቸው በፍትወት ግሎ ። የቢራ

ጠርሙሷን በግራ እጃቸው ይዘው ፣ በቀኝ እጃቸው የቤቱን በር የውስጥ መቀርቀሪያ ዘንግ ከጥግ በኩል እነሱና "አልጋው ላይ ውጣ!" አሉት ።

በሩን አጥብቀው ዘግተው ፣ ሙሉ በሙሉ የሚሸፍነውን መጋረጃ ቁልቁል ለቀው ሲመለሱ ድንቃለም አልጋቸው ላይ ወጥቶ አላገኙትም ።

"አልጋው ላይ ውጣ እንጂ !" አሉት በአይናቸው ቂጥ እየተመለከቱት ።

ድንቃለም ዝም አለ ፣ ጠጉሩን እየቀነጣጠበ ። በሀሳብ ተግባቡ ።… እና ተላመዱ ። ወደዳቸው ። ዱቤ ሲጠይቅ አይከለክሉትም ። ምን ያህል መጠጣት እንዳለበት ወስኖ አያውቅም ። ከወይዘሮ ባፈሳና ጥቁር ጠላቸው የሚገላግለው ሰአት እላፊ ሆነ ። ያራት ኪሎን ጥበቃ ጓዶች እንደ ጉድ ስለሚፈራቸው ውስጥ ውስጡን እያሳበረ ቤቱ ይገባል ።

ዛሬ ግን ወይዘሮ ባፈሳ "ጥቁር ጠላ የለም !" ብለውታል። ስለሆነም ጥቁር ጠላ ፍለጋ ይዘዋወራል ።

• ሁለት እጆቹን ፣ ሱሪው ኪሶች ውስጥ ከቶ ሲዘዋወር በአካባቢው የሚገኙ ሴተኛ አዳሪዎች በራፋቸው ላይ እንደ ቆሙ ቃል ይጥሉበታል ። በዘዴ ይጠሩታል ። ወሲብ ይጋብዙታል ። አየት አድርጐአቸው ያልፋል ፤ ጥቁር ጠላ ፍለጋ አይኖቹን ግራ ቀኝ እያማተረ ።

"ጂሚ!" አለችው አንዷ ሱሪ የታጠቀች ።

ጥቁር ጠላ የተሞሉ ጠርሙሶች ለአላፊ አግዳሚው እንዲታይ ሆነው የተደረደሩባት አንዲት ጠባብ ክፍል በር ላይ የተገተረች ወጣት ነበረች ። ያን እንደተመለከተ ሳያመ



ነታ ጥልቅ አለ ።

"ምን ልታዘዝ?" አለችው ገና ተደላድሎ ሳይቀመጥ ።

"ምን ምን አለ?" አላት ከጥቁር ጠላ በቀር ሌላ ምርጫ ያለው ይመስል ።

"ጥቁር ጠላ ፣ የአበሻ አረቂ ፣ አፕሬቲፍ …"

"አፕሬቲፍ ! እንዴት ?" ግራ ገባው ።

"አፕሬቲፍ አያውቁም?" ፈገግ አለች ።

"እንዴት አልኩሽ? ምን ያስገለፍጥሻል?"

"አፕሬቲፍ ማለት ጥቁር ጠላና የአበሻ አረቂ ተደባልቆ ማለት ነው ። ሌላ ስም አለው እንዴ?"

"ጥቁር ጠላውን ስጭኝ!" አላት ሲጋራ እያወጣ ።

ጋዜጠኛው ድንቃለም ሚስት ድስት የሚባል ነገር የለውም ። የዛሬ ሶስት አመት ግን ነበረው ። ኢየሩሳሌም የምትባል ሚስትም ነበረችው ። ኢየሩሳሌም አንበሴ ፣ የፍራሽ ተራው ጆንበሴ ማን ችሎት የበኸር ልጅ ። ጥሩ ትዳር ነበረው ። ግን አልዘለቀለትም ።

አለቆቹ ጋር የማይግባባና በጥሩ አይን የማይመለከቱት፣ ራሱን ከሙያውና ከወቅቱ ጋር ማጣጣም የተሳነው በመሆኑ ዘወትር ብስጩ ነበር ። ኢየሩሳሌም ደግሞ ችግሩን አትረዳለትም ። ሲበሳጭ አታስክነውም ። በብቸኝነት ባህር ውስጥ ሰጥሞ ሲንከላወስ አይዞህ አትለውም ። ሃሳቡን እንዲያካፍላት አትወተውትም ። አታግባባውም ። እሷም በሀሳብ ጭልጥ!… ቤቱ ድብርት ወረረው ። ቤቱን መጥላት ሲጀምር እሷም እንደዚያው ። ለሷ የነበረው ፍቅር በመቀነስ ላይ ያለ እየመሰላት ፣ ራሷ በፈጠረችው ጥርጣሬ ትዳሯ አስጠላት ።

ማታ ለአልጋ ላይ ይገናኛሉ ፤ በቃ ። የአልጋ ላይ ልፊያቸው ከቀረም ወራት አስቆጠሩ ። ከአንገት በላይ ብቻ ያወራሉ ። ያም ገደብ አለው ።

ደመወዙን ተቀብሎ ፣ የወር ወጭ በሰጣት የጥቅምት ወር የመጀመሪያ ሳምንት ላይ ግን የከረረ ጠብ ገጠሙ ።…

"እራት የለም እንዴ ኢየሩስ?" ምንም ሃሳብ ቢገባውና ቢበሳጭም ባለቤቱን 'ኢየሩስ!' ብሎ ከመጥራት ታቅቦ አያውቅም ፤ ስሟን መጥራት አስፈላጊው ከሆነ ።

"የለም!"

"ለምን?"

"ለምን ራሱ ጥያቄ ነው!"

"መልስ ግን ሊሆን አይችልም ?"

"ሊሆንም ላይሆንም ይችላል ።"

"እራት ለምን የለም?"

"ራስህ ሰርተህ ለምን አትበላም?"

"እንደዚህ አይነት ጥያቄ ከአፍሽ ወጥቶ እንደማያውቅ ልቤ እያለሽ!"

"የወጥ ቤትና የጓዳ ስራ ለኔ የፈረደብኝ ማነው?"

"ከዚያች ቀልቃላ የቀበሌ ሴቶች ሊቀመንበር ጋር መዋል እንደጀመርሽ መች አጣሁት! ኖ ማተር ።"

"ለማያውቅህ በለው! ሆ…ሆ!… አንተስ ማን ጋር እየዋልክ ነው? ሀና አታበላህም እንዴ ? ወይስ የማድ ቤት ስራ አይሆንላትም ?" ሳቋን ለቀቀችው ፣ የንዴት ሳቅ ።

"ሀና!…ሀና ገብረመድህንን ማለትሽ ነው?"

"ባክህ ዝጋ! ኢየሩሳሌም መደበሪያህ አይደለችም ።



ከሀና ያነሰ ቁንጅና ካለኝ ሞቴ ነው!… ለዚያች በስባሳ ደግሞ!" ብላው ምራቋን ጢቅ አደረገችበት ።

"ለምን እንዲህ ትያለሽ ? እኔ ለአንቺ ግልፅ ያልሆንኩበት ጊዜ አለ? ለምን አትጠይቂኝም?"

"ምን ብዬ ነው የምጠይቅህ? እንዴት እንዳወጣሀት ፣ እንዴት እንደምትላፉ…ነው? ሰው አታውቅምና!"

"እኔ ላንቺ ግልፅ ሆኜ አላውቅም?"

"ግልፅነትህን !! ሞኝህን ብላ ! ዝንተ አለም ስታሞኘኝ ልትኖር ነው?"

"ሃቁን ልንገርሽ! ሀና የስራ ባልደረባዬ ናት ። አንድ ቀን ፓርቲ አዘጋጅታ ጠራችን ፤ ሄድን ፤ እንዴት እንደሆነ አላውቅም ፤ ሌሊቱን እሷ ጋር አድሬአለሁ ። በቃ! …ብዙ ጠጥቼ ነበራ! ከዚያ ወዲህ በወሲብ አታውቀኝም ፣ አላውቃትም ። በርግጥ ይህን አልነገርኩሽም…"

አላስጨረሰችውም ። "የሷን ለምን ደበቅከኝ?"

"ረስቸው ይሆናላ! ሌላ ብዙ ችግር አለብኝ አይደል?"

"ግንኙነታችሁ ቢቀጥል እንጂ!… ሀናን ለፍቅር ፣ ኢየሩሳሌምን ለመደበሪያ !" አስካካችበት ፣ ፀጉሯን በንዴት ጨምድዳ ።

"ታዲያ ችግሩ እራት ባለመስራት ይፈታል?"

"ምን ታደርገዋለህ!"

"አኬ !… ከእንግዲህ እንዳሻሽ ልትፈነጭብኝ አትሞክሪ" አላት ተቆጥቶ ። "ፍቺ ከፈለግሽ አልጋዬንና ጠረጴዛዬን ከነመፃህፍቶቼ ትተሽልኝ ውልቅ ማለት ትችያለሽ ።

መነፍረቅ ጀመረች ።…

በበነጋው ከስራ ሲመለስ ብቤት ውስጥ ያገኘው አልጋ ውን ፣ ጠረጴዛውን ፣ ወንበሮቹንና መፃሕፍቱን ብቻ ነበር ።

በባዶ ቤት ሁሉ ነገር ስላስጠላው ወደ ድራፍት ቤት ጐራ አለ ። በዚያን ጊዜ ለዚያ የሚሆን ገንዘብ አላጣም ነበር ። ከዚያም በኋላም ወደ ድራፍት ቤት ። …በብድር ድራፍት… እየተበደረ ድራፍት… የሚያበድረው ሲያጣ ወደ ጥቁር ጠላ! …በዱቤ ጥቁር ጠላ…ዱቤ! ዱቤ! ዱቤ!… የታዋቂው ጋዜጠኛ ኑሮ ።…

የዛሬው ጥቁር ጠላ እንደ ወይዘሮ ባፈሳ አፍ የሚሞላ ሆኖ የመጠጥ ልክፍቱን ባያስወርፍለትም የቤቷ ፀጥ ማለት ግን አስደስቶታል ። ጥቁር ጠላ እየጠጣ ብቸኛ መሆን ለሚፈልግ የምትመረጥ አይነት ናት ።

"ልጨምር ጋሼ?" ባዶ ጠርሙስ ከፊቱ እያነሳች ።

"ምን ይመስልሻል?"

"እኔ ምን አውቄ ጋሼ!"

"ባንቺ ውሳኔ እመራለሁ ብልስ!"

"ስእቱ ገና አንድ ተኩል ነው ። ቢጨምሩ ይሻላል ።" አንድ ጠርሙስ ጥቁር ጠላ አመጣችለት ።…

ድንቃለም ከጋዜጠኛነት ሙያው ከተራራቀ ሳምንታት አልፈዋል ። በሙያው እያፈረበት መጥቷል ። "ጋዜጠኛ ፣ መንጋ ግድም ባለስልጣን እንደፈለገ የሚያሾረው ፣ እንዝርት ነው!" ይላል ለራሱ እየደጋገመ ።

በአማርኛ ቋንቋ በዲግሪ ተመርቆ ፣ በፕሬስ መምሪያ ውስጥ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደ ተመደበ ደስተኛና



በአፍላ የወጣትነት ጊዜውም 'ጋዜጠኛ' ሲባል ኩራት የሚሰማው ሰው ነበር ። ለሙያው የነበረው ክብርና የሚያሳ የው ስነምግባርም ጥብቅ ነበር ።

የኋላ ኋላ ግን አለቆቹ የሱን ችሎታ እየተጠቀሙ ፣ የስራ ውጤቶቹን በባለቤትነት ለበላይ አለቆቻቸው እያቀረቡ ሲመሰገኑበት ፣ ሲሾሙበትና ሲሸለሙበት መታዘብ ጀመረ ። ቅሬታ እየገባው መጣ ። በመጨረሻም የቅርብ አለቃው ጋር አለመግባባት ተፈጠረበት ።…

"አቶ ድንቃለም! ካሁኑ ስራህ በተጨማሪ ርእስ አንቀፅ እያዘጋጀህ እንድታቀርብ ወስነናል ። ከዛሬ ጀምሮ እሱን ደርበህ ትሰራለህ ።!"

"እስከዛሬ የተመደበበት ሰውስ?"

"እሱ አይመለከትህም!"

"እንግዲያው እኔም አይመለከተኝም ። ከአቅሜ በላይ ነው ፣ አይሆንልኝም!"

"አይሆንልኝም ስትል አጥር እየጣስክ መሆኑን ታውቃ ለህ?"

"ጋዜጠኛ ሲባል'ኮ ወረቀትና ቀለም እየጐረሰ ፅሁፍ የሚያመርት ፋብሪካ አይደለም ። ጋዜጠኛ በሚያምንበትና በሚመስጠው ርእስ ጉዳይ ላይ ማተኮር አለበት ። አለበለዚያ ጋዜጠኛ መሆኑን አቁሟል። ራፖርር ፀሃፊ ሆነ ማለት'ኮ ነው?"

"ጋዜጠኛነት ያረጀንበት ነው ። 'ኋላ የመጣ አይን አወጣ!' አሉ ። ጋዜጠኛነትን ለኛ ነው የምታስረዳን? ለፓርቲ ዲሲፕሊን አትገዛም?"

በተለይም ለኋለኛው ጥያቄ የሚሆን መልስ አልነበረ

ውም ። ከባድ ዝምታ ዋጠው ።…

ከዚያ ጊዜ በኋላ በአለቆቹ የቂምና የጥርጣሬ መነፅር ውስጥ ገባ ። ያዘዙትን ይፈፅማል ። ያልተደረገውን እንደተደረገ አድርጎ እንዲፅፍ ይታዘዛል ። ቢያምንበት ባያምንበት መፈፀም ግዴታው ነበር ።

ከስራ ባልደረቦቹ ውስጥ ደግሞ ተጠላፊዎቹና ጠላፊዎቹ በዝተዋል ። እሱ ከተጠላፊዎቹ ነው ። የራሱንም ሆነ ጠቅላላ ተጠላፊ ጋዜጠኞች ሁኔታን ሲያስተውል "ጋዜጠኛነት ወሬ ኮማሪነት ፣ ጋዜጠኛ ወሬ ኮማሪ!" ማለት ጀመረ ፣ ከራሱ ጋር ሲወያይ ።

ጠልፎ በመጣል በኩል ደግሞ ግራ ኮሌታው ላይ የሌኒንን ምስል የሚለጥፈው አንድ አይናው አምደ ማርያምን የሚያክል ማንም አልነበረም ፤ በብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ህንፃ ውስጥ ።

አምደ ማርያም አንዳንድ ጊዜ 'የቃላት ትራፊክ!" እየተባለ ይጠራ ነበር ። ታዲያ ፌቱ አይደለም ። የሚተማመኑቲሰባሰበው እንደዋዛ ሲያወሩ ነው ። ቃላትን ከቃላት እያዋጋ ብዙዎችን ለችግር የዳረገ ነው ይባላል  በሌለበት ። በ69 አመተ ምህረት አካባቢም በሌኒን ስም ይምል እንደነበር ይነገራል ።

አንድ በሞንም አምደ ማርያም የድንቃለም አለቃ ሆኖ ነበር ። በዚህ የስራ ዝምድናቸው ምክንያት ድንቃለም ያዘጋጀው  ፅሁፍ እንዲፀድቅለትና ወደ ህትመት እንዲላክ ለአምደማርያም ያቀርባል ።

"ኢትዮጵያ ስትል ምን ማለትህ ነው?" ይለዋል አምደ



ማርያም ፤ አንድ ቀን ።

"ኢትዮጵያ ስል ያው የምናውቃት ኢትዮጵያን ማለቴ ነዋ!" ድንቃለም በአጭር ይመልሳል ፤ የአምደ ማርያም አመጣጥ እየገባው ።

"አባባሌን ግልፅ ላድርግልህ! ኢትዮጵያ ስትል የትኛዋን ኢትዮጵያ ማለትህ ነው ? አሻሚ ነገር'ኮ ሆነ ። እኛ ጋዜጠኞች ነገሮችን ግልጥልጥ አድርገን ፤ ሀቅን አፍረጥርጠን መፃፍ አለብን ። የጋዜጠኛ መዝገበ ቃላት በጣም ትልቅ ነው ። የጋዜጠኛ ዋና ካፒታሉ ቃላት ናቸውና!…"

"ኢትዮጵያ ስል ይቺ ኢትዮጵያ ማለቴ ነው" ብሎ በንዴት ወለሉን በጫማው መታ መታ አደረገና "ኢትዮጵያ ተብሎ የሚጠራ ሌላ አገር ስለሌለ ለምን አሻሚ ይሆናል?" አለው ።

"አልገባህም ! የምልህን በፖለቲካ አይን ብታየው ። ሌኒን ሁሉን ነገር በፖለቲካ አይን ማየት ይወድ ነበር ይባላል።" ከንፈሩን መጠጠ ። ቀጠለና "ለምሳሌ ውሀን እንውሰድ ። እኛ የምንጠጣውን ውሀና ታሪካዊ ጠላቶቻችን የሚጠጡትን ውሀ በእኩል አይን ትመዝነዋለህ?" በሀሳቡ ያሸነፈ ይመስል የዛጉ ጥርሶቹን እያሳየው ሁለት እጆቹን ዘረጋለት ። "አቶ ድንቃለም! ኢትዮጵያ አንዲት ብትሆንም ብዙ ናት!"

"አልገባኝም!"

"አትቸኩል፤ ሀቀኛ ጋዜጠኞች አይቸኩሉም። አዲሲቷ ኢትዮጵያ ፣ የፊውዳሎች ኢትዮጵያ ፣ የወያኔ ግንጥልጥል ኢትዮጵያ ፣… መልኳ ብዙ ብዙ ነው ። እና ግልፅ ይደረግ!